


የቀጨኔ ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን

ዋጋው ፪ ብር

# « ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ »



ጥንታዊቷና ታሪካዊቷ ርእሰ ርኡሳን የመርጡለ ማርያም
ቤተ ክርስቲያን

ቊጥር ፫

መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፹፮ ዓ/ም

አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት፡ ታሪክና ባሕል፡ የመንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ዜና ለሕዝበ ክርስቲያን የሚያቀርብ ስለሆነ ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ» ተብሎ ተሠይሟል ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ኮሚቴ እየተዘጋጀ በየወሩ አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

ዋና አዘጋጅ ሊቀ ልሳናት ነቅዐ ጥበብ ወንድም
ረዳት አዘጋጅ መ ኤፍሬም በየነ

ስልክ 11 26 63
የመልእክት ሣጥን ቍጥር 1283
አዲስ አበባ

# የጥያቄና መልስ ዓምድ

ለልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ መጽሔት አዘጋጅ

አዲስ አበባ ፤

ከሁሉ አስቀድሜ የከበረ ሰላምታየን አቀርባለሁ ከሰላምታየ ቀጥሎ የማቀርበውን ጥያቄ እንደ ምትመልሱልኝ እምነቴ የጸና ነው ።

ፍጥረታት በሙሉ ስንል በሰማይና በምድር ያሉትን በማጠቃለል መሆኑ አይካድም ነገር ግን ያልገባኝ ቢኖር ኪሩቤል ወይም አርባዕቱ እንስሳ መቼ እንደተፈጠሩ እንዲያብራሩልኝ በትሕትና እለ ምናለሁ ።

ኃይለ ልዑል ከወሊጋ ፋይናንስ ቢሮ

— የመላእክት ተፈጥሮ በቀዳማይ ሰዓተ ሌሊት በዕለተ እሑድ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ያስ ረዳሉ ኪሩቤልም የተፈጠሩት በዚሁ ቀን ነው ።

ኪሩቤል ወይም ሱራፌል የነገድ ስም ነው የኪ ሩቤል አለቃ ቅዱስ ገብርኤል ሲሆን የሱራፌል አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ነው ።

ይህንንም ስለ ስነ ፍጥረት የተጻፉ መጻሕፍት ንና አክሲማርስ የተባለውን መጽሐፍ እንዲሁም በሊቃውንቶቻችን የተጻፈው ሥርወ ሃይማኖት የተ ሰኘውን መጽሐፍ ቢመለከቱ በይበልጥ ይረዳሉ ።

ለልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ መጽሔት አዘጋጅ ፤

አዲስ አበባ

ለጤናችሁ እንደምን አላችሁልኝ እያልኩ የከበረ ሰላምታየን አቀርባለሁ ።

ወገኖቼ በእግዚአብሔር ፈቃድ የጀመራችሁትን ልሳነ ተዋሕዶ የተሰኘውን መጽሔት ከሰው እጅ በአነበብኩት ጊዜ ነፍሴ በኃሤት ተሞላች እምነት በሥራ ማለት ይህ ስለሆነ በርቱ ተበራቱልን መጽሔቱ ወደ ክፍላተ ሀገር እንዲሠራጭ ጥረት አድርጉልን ፤

ስለዚህ ቀጥሎ ያቀረብኩትን አስተያየት እንዳ ሳታስቀሩ እንደምታወጡልኝ እምነቴ የጸና ነው ።

## የእውነተኛ ክርስቲያን እምነት

ሀ— ነፋስ እንደሚወዘውዘው ሸምበቆ ወዲያና ወዲህ የሚዋልል ሳይሆን ጥብቅ መሆን አለበት

በሰላም ዘመን አምና በቆየው እምነቱ ችግርና መከራ በደረሰበት ጊዜ በዚያው መጽናናት እንጂ መናወጽ አይገባውም ።

ለ— እምነት ሙሉ እንጂ ጎደሎ መሆን አይገ ባውም እያንዳንዱ ሰው ቅድስት ቤተክርስቲያናችን የምታስተምረንን የሃይማኖት ትምህርቶች ሁሉ ማመ ን አለበት እንጂ ብዙውን አምኖ ጥቂት ቢተው እም ነቱ ከንቱ ይሆናል ።

ከአንድ የግንብ ቤት አንድ ድንጋይ ወይም ሸክላ ቢያነሱለት በተነሳው ምክንያት ቀስ በቀስ ቤቱ ስለሚቦረቦር ይወድቃል ከእምነቱና ከምግባሩ የጎደለ ሰውም እንደዚሁ ነው ።

ሐ— እምነት በሥራ መገለጽ አለበት እምነት ያለ ሥራ ጥቅም አያስገኝም በፍቅር መንፈስ በመመ ራት ርዳታ ስለሚያስፈልጋቸው ሰዎች የሚደረገው የተቀደሰ ሥራ እምነትን ከፍ ሊያደርገው መሠረ ቱንም ሊያጸናው ይችላል ።

ሐዋርያው ያዕቆብ «ከእምነት ጋር ሥራ አስ ፈላጊ መሆኑን ሲያረጋግጥ እንዲህ ይላል» ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው ›ያዕ ፪ ፤ ፳፮

መ— የማንኛውም ሰው እምነት ከመጠራጠር ፤ ከማሟረትና ከተሳሳቱ ሥራዎች ፈጽሞ መራቅ አለ በት የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ን ትምህርት በማስ ተማር የቀደሙና ዛሬም ያሉ መንፈሳውያን አባ ቶች ቀጥተኛ እምነታችንን ላልሰሙት አስምተው እስከ ዘመናችን ድረስ አቆዩን እኛም ከእነሱ የተረ ከብነውን እምነታችንን ላልሰሙት የነፍሳቸውን ደኅንነት ለማግኘት እንዲችሉ በማሰማት ለሚከተ ለው ትውልድ ማስረከብ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተጣለብን የተቀደሰ ሥራ ነው ።

ለሁሉም እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን ወንድማችሁ አሰፋ ቀልቤሳ ከም/ወለጋ ግምቢ

— ስለአቀረቡልን አስተያየት እናመሰግናለን

www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# ለሁሉም ዝግጅት ያስፈልጋል ።

ትጉሕ ገበሬ ወደ እርሻው ከመሔዱ በፊት አስፈላጊ የሆኑትን መሣሪያዎች ሳያዘጋጅ ሥራ መጀመር እንደማይቻል ስለሚያውቅ አስቀድሞ ይዘጋጃል ።

የማስተማር ችሎታና ልምምድ ያላቸው መምህራንም በቃልም ሆነ በጽሑፍ ትምህርት ለመስጠት በሚያስቡበት ጊዜ ትምህርቱን የሚቀበሉት እነማን እንደሆኑ ሳያውቁና ሳይዘጋጁ እንደ ፈለጋቸው የዕውቀት አድማሳቸውን አይዘረጉም ።

በቤተ ክርስቲያናችንም የተማሩትም ሆኑ በመማር ላይ የሚገኙት ካህናት ለአገልግሎት ከመሔዳቸው አስቀድሞ የዕለቱን ስብሐተ እግዚአብሔር ሳይመለከቱ አይሔዱም ።

በዚሁ አንፃር የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ ክርስቲያኖች መመህራን የሚያስተምሩትን ቅዱሳት መጻሕፍት የሚናገሩትን ቃል በተግባር ለመተርጎም መዘጋጀት ያስፈልጋል ።

እግዚአብሔር ወልድ ዳግመኛ ወደዚህ ዓለም እንደሚመጣና በሰዎች ፊት እንደሚገለጥ በቅዱሳት መጻሕፍት ተነግሯል ግን ዘመኑና ጊዜው መቼ እንደሆነ ከእግዚአብሔር በቀር ማንም የሚያውቅ ስለሌለ ሰዎች በማያስቡበትና በማይጠረጥሩበት ዕለት እንደሚመጣ አውቀው ሊዘጋጁ ይገባል ።

ስለ ዳግም ምጽአት በብሉይና በሐዲስ ኪዳናት የተነገሩትን ምልክቶች የምናስታውስባቸውና የምንመረምርባቸው ሳምንታት ሀ/ በዓቢይ ጾም ደብረ ዘይት ለ/ ወርኃ ጽጌ ሐ/ ከወርኃ ጽጌ በኋላ በሚሆነው አስተምህሮ የመጨረሻው እሑድ አልፎ አልፎ ስለሚያገኝ ይታሰባል ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረ ዘይት ተራራ ተቀምጦ ሳለ ደቀ ዛመሙርቱ የመምጣትህ ምልክት ምንድነው ? ብለው ሲጠይቁት "ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና ብዙዎችንም ያስታሉ ብሏል» ማቴ ፡ ፳፬ ፡ ፫ ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ክርስቶስ ዳግመኛ የሚመጣበት ዘመን ሲቀርብ "ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ የማያመሰግኑ ፍቅር የሌላቸው ሐሜተኞች ራሳቸውን የማይገዙ መልካም የሆነውን የማይወዱ ከዳተኞች ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላ የሚወዱ ይሆናሉ ሲል በ፪ኛ ጢሞቴዎስ መልእክቱ በም ፡ ፫ ፡ ከቁ ፡ ፩—፮ ፡ ያስተምረናል ።

የመድኅን ክርስቶስ አመጣጥ ከቀድሞው አመጣጡ የተለየነው የቀድሞው አመጣጥ ራሱ መሥዋዕት ሆኖ ዓለምን ለማዳን ነው የኋለኛው አመጣጥ ግን መልካም ለሠራ በቃሉ ለአመነና በሕጉ ለፀናዋጋ ለመስጠት ሕጉን ላልፈጸመ ፍርድ ለመስጠት ነው ።

የቀድሞው አመጣጡ ኃጥአንን በንስሐ ለመጥራት የጠፉትን ለመፈለግ የተጎዱትን ለመርዳት የተበተኑትን ለመሰብሰብና ለማዳን ነበር ። ዳግመኛ ወደዚህ ዓለም የሚመጣው ግን ለፍርድ ስለሆነና የሚመጣበት ሰዓት ስለማይታወቅ የሰው ልጆች ሁል ጊዜ ተዘጋጅተው መጠበቅ ይኖርባቸዋል ።

ዓለምን የፈጠረና ዓለምን አሳልፎ የሚኖረው መድኅን ክርስቶስ በማይታበል ቃሉ "የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ስለሚመጣ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ" ሲል አስተምሯልና ።

# የመጽሐፍ ቅዱስ ቀን በዓል ቅዱስ ፓትርያርኩ በተገኙበት ተከበረ

ዓለም አቀፋዊ ባሕርይ ካላቸው አንጋፋዎቹ የብሪታንያና የአሜሪካ የመ/ቅዱስ ማኅበራት ጋር የተያያዘ ጠባይ ያለው የኢትዮጵያ መ/ቅዱስ ማኅበር ለመጀመሪያ ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ቀን "በሚል ያዘጋጀው በዓል ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በተገኙ



ቅዱስ ፓትርያርኩ በዓሉን በጸሎት ሲከፍቱ

በት የካቲት ፳፮ ቀን ፲፱፻፹፮ ዓ/ም በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተከብሯል ።

የበዓሉ ዋና ዓላማ ሰዎች የማኅበሩን አቋምና አገልግሎት በውል አውቀው ፣ ለማኅበሩ በሚያደርጉት የገንዘብና የቁሳቁስ (የማቴሪያል) ድጋፍ የእግዚአብሔር ቃል ለሁሉ እንዲዳረስ የአብያተ ክርስቲያናትንና ምእመናንን ተሳትፎ ለማጠናከር መሆኑ ታውቋል ።

በስነ በዓሉ ላይ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳት ፣ የመካነ ኢየሱስ ፕሬዚዳንት ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ፕሬዝዳንት ፣ የቦርድ አባላትና ጠቅላይ ጸሐፊ ፤ ሌሎችም የክርስትና እምነት ድርጅቶች መሪዎችና አባላት ጥሪ የተደረገላቸው አምባሳደሮችና ዲፕሎማቶች የአዲስ አበባ አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎች እንዲሁም ቁጥሩ በርከት ያለ ሕዝብ ተገኝቷል ።



የልዩ ልዩ ሃይማኖት አባቶችና የልዩ ልዩ ድርጅቶች ኃላፊዎች በበዓሉ ላይ እንደተገኙ

በመርሐ ግብሩ መሠረት ጉባኤው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ጸሎትና ቡራኬ ተከፍቶ የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና የማኅበሩ ተጠሪዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበርንና የዕለቱን በዓል የተ

ተከታዩን በ፲፭ኛው ገጽ ይመልከቱ

www.ethiopianorthodox.org

# ቃል ሥጋ ኮነ

ተፀነሰ ለማለት ፀቅድምና ነበር ማለት ጥንቱ ነው በቅድምና ፤ ዓለም ሳይፈጠር የነበረው ያ ቃል ሥጋ ሆነ ሲል ቅዱስ ዮሐንስ በጻፈው ወንጌል ገል ጾታል ዮሐ ፩-፲፬

አዳም ሕገ እግዚአብሔርን በመተላለፍ በደ ረሰበት መከራ ሲያዝንና ሲያለቅስ ሳለ ቸርነት የባ ሕርዩ የሆነ አምላክ «በሐሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ ወእድኅከ ውስተ መርኅብከ ወእትቤዘወከ በመስቀልየ» አም ስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ከሰማየ ሰማ ያት ወርጄ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ ተሰቅዬ ሙቼ ሥጋየን ቆርሼ ደሜን አፍስሼ አድንኃለሁ ሲልተ ስፋ ሰጠው ።

ለአዳም የተሰጠው የተስፋ ቃል የሚፈጸምበት ዘመን በጣም የራቀ ቢሆንም በፈጣሪ ዘንድ አልተ ዘነጋም ፤ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ የተነ ሡት ሰዎች ሁሉ የተነገረውን የተስፋ ቃል ለልጆ ቻቸው በቃላቸው እየተናገሩ እያሌ ዘመን ኑረዋል ፤ በዘመነ ሙሴ ግን ቃል ሊቃል እየተነገረ የመጣው ተስፋ በጽሑፍ መስፈርና መሠራጨት ጀምሯል ፤ ነቢያትም እየተነሡ ሱባኤ ቆጥረዋል ፤ ምሳሌ መስ ለዋል ፤ ትንቢትም ተናግረዋል ።

ሙሴ የእግቱን የካህን ምድያም የዮቶርን በጎ ች በደብረ ሲና ተራራ ጥግ እሠማርቶ ሲጠብቅ ነበ ልባል ከሐመልማል ጋር ተዋሕዶ ሲጨስ ተመለ ከተ ቦታው በጣም እሩቅ ስለነበር በጎቹ እንዳይጠ ፉበትና አውሬም እንዳይበላባበት ከፈረሰ ግንብ ውስጥ አስገብቶ ዘግቶባቸው ሄዶና ቀረብ ብሎ ቢመለከት ነበልባሉ ሐመልማሉን ሳያቃጥለው ሐመልማሉም ነበልባሉን ሳያጠቁረው አገኝቶታል ፤ ይህ ም ነበል ባል የመለኮት ሐመልማል የትስብእት ምሳሌ ሲሆን አምላክ ሰው ሲሆን ሥጋን ሲለብስ ባሕርየ መለኮቱ አለመለወጡን የሚያስረዳ ነው ።

የአምላክ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ሰው መሆን በመ ንፈስ ቅዱስ ተገልጾላቸው ትንቢት የተናገሩ ነቢ ያት ብዙ ሲሆኑ ለማስረጃ ያህል ጥቂቶቹን ቀጥለን እንመለከታቸዋለን ነቢዩ ኢሳይያስ «እነሆ ድን ግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙ ንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች ፤ ከዕሤይ ግንድ በትር ይወጣል ከሥሩም ቁጥቋጦ ያፈራል በማለት ተናግሯል ኢሳ ፯-፲፬ ፡ ፲፩-፩ ። ሕዝቅኤልም ወደ ምሥራቅም ወደሚመለከተው በስተውጭ ወደ አለው ወደመቅዱሱ በር አመጣኝ ተዘግቶም ነበር እግዚአብሔርም ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አም ላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል በማለት ተናግሯል ትን ሕዝ ፵፬-፩ ነቢዩ ኤርምያ ስም» እርሱ ራሱ ሰው ሆኖ ወደዚህ ዓለም ይገባል እኔ ሰው ሁኖ ያየሁት ከባሕርይ አባቱም ወደዚህ ዓለም የተላከ ፤ ሰው ሁኖም ወደዚህ ዓለም የመጣ እርሱ አብሯቸው ይታይ ዘንድ ይገለጥላቸውም ዘንድ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያትን ለእርሱ አገልጋዮች ሲሆኑ ይመርጣል ለማስተማርም ወደ ደብረ ዘይት ይወ ርዳል የተራበችንም ሰውነት ሁሉ ያጠግባል ብሏል ተረፈ ኤር ፲፩-፵፪

የተነገሩት ትንቢቶች ለመፈጸም በተቃረቡ ጊዜ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልኮ ወደ እመቤታችን ድንግል ማርያም መጣ እመ ቤታችን በወላጆቿ ቤት ሦስት ዓመት ከቤተ መቅ ደስ ፲፪ ዓመት በጠቅላላ ፲፭ ዓመት ከኖረች በኋላ ከቤተ መቅደስ ወጥታ በጻድቁ በዮሴፍ ቤት ተቀ ምጣ ነበር ለዮሴፍም የተሰጠችው እንዲያገለግላት ፤ እንዲላላካትና እንዲጠብቃት ነው ።

አረጋዊው ዮሴፍ ድንግል ማርያምን ለማገል ገል ከተቀበላት በኋላ ከቤቱ አስቀምጧት ለንግድ ወደሩቅ ሀገር ሔደ ፤ እርሱዋም እንስራዋን ተሸክማ ውኃ ልትቀዳ ሔደች ቀድታ እንስራዋን ስትሸከም የተጠማ ውሻ ውኃ ፍለጋ እየተርገበገበ ደረሰ ከዚያ የነበሩ ሴቶች አላዘኑለትም በበትርና በደንጊያ ይደ በድቡት ጀመር ድንግል ማርያም ግን ለሁሉም ፍጥ ረት ርኅርኅተ ልብ ናትና እንስራዋን ከጀርባዋ አው ርዳ ከእንስራዋ አጉድላ በወርቅ ጫማዋ ላይ በማፍ ሰስ የተጠማውን ውሻ አጠጣችው ከዚያ የነበሩ ሴቶች እንስራዋን በማጉደሏ ሲዘባበቱባት ወዲያው የጎደለው እንስራዋ በተአምራት ሞልቶላት ስት ሸከም መልአኩ ትጸንሻለሽ አላት ።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም አ ባቷ አዳምን እናቷ ሔዋንን ያሳተ ሰይጣን እኔንም ሊያስተኝ ነው ? ብላ ዝም ብላ መንገዷን ቀጠለች ፤ ከቤት ደርሳ እንስራዋን ስታወርድ በድጋሜ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ትፀንሲ / ትፀንሻ ለሽ ስላላት የሰይጣን እንዳልለው ደጋገመኝ ደግን ነገር መረዳት የሚቻለው ከቤተ መቅደስ ነውና ወደዚያው ሄጄ ልረዳው ብላ ከደናግለ እስራ ኤል ጋር ተካፍላ የምትፈትለው ሐርና ወርቅ ነበራት ያንን ወስዳ ከቤተመቅደስ በወንበር ላይ ተቀምጣ ሐሩንና ወርቁን እያስማማች ስትፈትል ለሦስተኛ ጊዜ ቅዱስ ገብርኤል መጣና ጸጋን የተ መላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር ከአንች ጋር ነውና እነሆ በድንግልና ጸንሰሽ በድንግልና ትወ ልጃለሽ አላት «ወርዕያ ደንገፀት እምቃሉ»እንዲል

ተከታዩን በ፲ኛው ገጽ ይመልከቱ



# ቅዱስ ፓትርያርኩ የቀጨኔ ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ያሠራቸውን የሙዝዬምና ክሊኒክ ቤቶች መርቀው ከፈቱ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የቀጨኔ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት ያሠራቸውን የሙዚዬምና ክሊ ኒክ ቤቶች መጋቢት ፲፯ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ/ም ከሰዓት በኋላ መርቀው ከፍተዋል ።

በደብሩ ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት የቀረበው ዘገባ እንደሚያስረዳው የቤተ ክርስቲያኒቱ ጥንታዊና ዘመ ናዊ ቅርሶች ማስቀመጫና ቀድሞ የመካነ መቃብር የነበሩ ቦታዎችን ከመቃብር ቤቶች ተጠሪዎች ጋር በመስማማት አስተካክሎ ለዚሁ አገልግሎት እን ዲውል በማድረግ ታላቅና ግዙፍ የሆነ የሙዚየም ሕንጻ መሠራቱን ገልጿል ። እያይዞም ለክሊኒኩ አገ ልግሎት ይውላል ተብሎ ከተጀመረ በኋላ ሥራው ተቋርጦ ቆርቶ የቆሻሻ መጣያ ቦታ ሆኖ ቆይቶ የነ በረውን የሰበካ ጉባኤው በማሻሻልና በማስፋፋት ለሕሙማን የመኝታ ክፍል ለፋርማሲ (ለመድኃ



ቅዱስነታቸው የተሠሩትን የሙዝዬምና ክሊኒክ ቤቶች መርቀው ሲከፍቱ

ኒት ቤት)እና ለልዩ ልዩ የአገልግሎት መስጫ የሚ ውሉ ፯ ያህል ተጨማሪ ቤቶችን በመሥራት ጥሩ የክሊኒክ ሕንጻ እንዲሆን ያደረገ መሆኑን ከቀረ በው ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል ።

በተጨማሪም የዚሁኑ ክሊኒክ ጠቀሜታ በብዙ መልክ ለማየት ሲባልም የታወቁና የተለያዩ የሕ ክምና ባለሙያዎች ፫ ከፍተኛ ስፔሻሊስት ዶክተ ሮች እንዲከራዩት የውል ስምምነት ስለተፈረመ ለአካባቢው ሕዝብ እጅግ ጠቃሚ የሆነ የሕክምና አገልግሎት ማስገኘት እንደሚችል የታመነበት መሆ ኑን ገልጾ ኪራዩም የደብሩን ገቢ ለማዳበር የሚያ ስችል በመሆኑ ያአካባቢው ነዋሪ የሆኑ ድሆች በታ መሙ ጊዜ ከደብሩ በሚሰጠው ትእዛዝ ነጻ የሕክምና እርዳታ የሚያገኙ መሆናቸው ታውቋል ። ጽ/ቤቱ ከ፩ — ፮ በዝርዝር ካቀረባቸው የሥራ ውጤቶች ዋና ዋናዎቹ በቀደምትነት የተጠቀሱ ሲሆን ከቅኔ ማኅሌት እስከ መቅደስ ያለውን የቤተ ክርስቲያኑን ዙሪያ ወለል የሥጋጃ ምንጣፍ በማልበስ ፤

— መካነ መቃብር በጥሩ ሁኔታ አሠርቶ ምእመ ናን በመጠነኛ ዋጋ እንዲጠቀሙበት በማድ ረግ የደብሩን ገቢ በማሳደግ ፤

— የቤተ ክርስቲያኑ የአጥር ክልል በአምቦ ድን ጋይ ባሸበረቀ ግንብ እንዲታጠርና የዓጸደ ቤተ ክርስቲያኑ ውበት እንዲጠብቅ ጭምር በቤተ ልሔም አካባቢ አትክልት በመትከል ለምእመናን ማረፊያ እንዲሆን ያሠራና

- ጥንታዊ የነበረውን የስፌት መኪና አገልግ ሎቱን እንዲጀምር በማድረግ ባለሙያ እያ ቀረበ ይገኛል ።

— በውጭ አገር ወርቅ ያሸበረቀ የታቦት መጐ ናጸፊያ በሰባት ሺ ብር አሠርቷል ።

— ለመዘምራኑ ፳፬ ጥንግ ድርብ ባለው ተጨ ማሪ በልዩ ጥበብ አሠርቶ አገልግሎት ላይ አውሏል ።

ተከታዩን በ፳፫ኛው ገጽ ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

## የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ካለፈው የቀጠለ ።

አንዳንድ ሊቃውንት በግእዙ ሐዲስ ኪዳን «ትእምኀክሙ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ኀሪት እንተ ውስተ ባቢሎን ዘግብጽ ፤ ወማርቆስ ወልድየ » በእግዚአብሔር የተመረጡት ፤ በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ወንድሞቻችሁ የሆኑት ፤ በግብጽ ባቢሎን የሚገኙት ክርስቲያኖችና ልጀም ማርቆስ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል የሚለውን ሰላምታዊ ኃይለ ቃል መሠረት በማድረግ ቅዱስ ጴጥሮስ መልእክቱን የጻፈው በሮም ሆኖ ነው ። ሐዋርያው መልእክቱን የጻፈው በ፷፫ ዓ/ም ሲሆን ፤ በዘመናችን የመልከዓ ምድር አቀማመጥ ግን ከሞላ ጎደል በቁርከና በአካባቢዋ በሚገኙ አገሮች ተበታትነው ለነበሩ ከአይሁድ ወገን ክርስትናን ለተቀበሉ ክርስቲያኖች ጽር በጣም ታማኝና ተወዳጅ ደቀ መዝሙሩ ስልዋኖስ እጅ ልኮላቸዋል ። ፩ኛ/ ጴጥ-፭-፲፪—፲፫ ፤

የመልእክቱም መሠረተ ኃሳብ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ን አዳኝነቱን አምነው ለተቀበሉት ሁሉ የእግዚአብሔር አብ ጸጋ እስከ ዘለዓለማዊው ዓለም የማይጠፋ ተስፋ የሚያስገኝላቸው መሆኑን ከማብሠር ጋር ስለ ክርስቶስ ብለው መከራና ስቃይ ሲቀበሉ ፤ በእሳት ሲቃጠሉ ፤ በድንጋይ ሲወገሩ ፤ እገር ጥለው ሲሰደዱ ጸጋውና በረከቱ በድል አድራጊነት እንደሚያወጣቸው ያስረዳል ። ባቢሎን የተባለችውም ሮም ናት ። በዚያን ጊዜ በሮሜ ልዩ ልዩ ኃጣውእ ይሠሩባት ስለነበር በግብርዋ ባቢሎንን ስለመሰለች «ባቢሎን» አላት ብለው ይተረጉሙታል ። በታሪክ እንደተመዘገበው ባቢሎን የተባሉ ሦስት ከተሞች ታውቀዋል ። እነሱም ፦ ፩ኛ እስራኤላውያን የተማረኩበት በኤፍራጥስ ወንዝ ዳር ያለው ፤ ፪ኛ በግብጽ ምድር የሚገኝ የወታደሮች አምባ የነበረው ፤ ፫ኛ/ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማለትም በዚሁ መልእክት በምእራፍ ፭ የተጠቀሰው ባቢሎን የተባለው ሮም መሆናቸው ነው ።

፭ኛ/ የቤተ ክርስቲያን ስያሜ ፦

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎችና መተርጉማን ቤተ ክርስቲያን የሚለውን ቃል በትርጓሜ ዘይቤአቸው ሲያብራሩ ቤተ ክርስቲያን ማለት ልዑል እግዚአብሔር ግእዛን ካላቸው ፍጥረታት ማለትም ከመላእክትና ከሰዎች ጋር ያለው ግንኙነት ነው ይላሉ ። ከዚህም አባባል በመነሣት የቤተ ክርስቲያንን የታሪክ ዘመን በሦስት ደረጃ ይከፍሉታል ። የመተርጉማኑም አከፋፈል ፤

፩ኛ/ የመጀመሪያዩቱ ቤተ ክርስቲያን ሰው ከመፈጠሩ በፊት በዓለመ መላእክት የነበረችው «የመላእክት አንድነት»

ተከታዩን በ፲ኛው ገጽ ይመልከቱ

## ቃል ሥጋ ኮነ

ከ፱ኛው ገጽ የዞረ

ቃሉን ሰምታ ደነገጠች መልሳም እምዓይቴ ረከብኩ ዘከመዝ ብሥራተ እንበለ ዘርዕ እምድር እትወተ እንበለ ዘርዕ እምድንግል ፅንስተ እንደዚህ ያለውን የምሥራች ከየት አገኘሽው ምድር ያለ ዘርዕ እህልን ታበቅላለችን ሴትስ ያለ ዘርዕ ያለሩካቤ ፀንሳ ልጅን ለመውለድ ትችላለችን ? አለችው እመቤታችን ይህንን ማለቷ ነገሩን ሽታው ሳይሆን እኔ አላደርገውም እንደምን ይሆንልኛል ስትል ነው» ዘንተ ትቤ ድንግል በእንተ ዘኢዓርገ ሕሊና ዕጓለ እመሕያው ውስተ ልባ» እንዲል መልአኩም የአንች ፅንስ እንደሌሎች ሴቶች አይደለም መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል ኃይለ ልዑል ወልድም ሥጋሽን ይዋሐዳል ይለብሳል ከሦስቱ ግብራትም ይከለክልሻል «ወውእቱ ንጹሕ እምነ ፫ቱ ግብራት ዘውእቶሙ ዘርዕ ወሩካቤ ወአስሎተ ድንግል ና እለ ሥሩዓን በዕጓለ እመሕያው ወእሙራን በሙ እንዲል ። «እርሱ ከሦስቱ ሥራዎች ንጹሕ ነው እነርሱም በሰው ዘንድ የታወቁ ዘር ሩካቤ ጋብቻ ናቸው ።

ከአንች የሚወለድውም ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ተብለው ከሚመሰገኑት ከሦስቱ ቅዱስ አንዱ ነው ፤ እርሱም የልዑል እግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ ይባላል ፤ እነሆ ከዘመዶችሽ ወገን የምትሆን ኤልሣቤጥ እንኳን በፍጹም እርጅናዋ ልጅ ጸንሳለች ከጸነሰችም ስድስተ ወሯ ነው ፤ አንችም በድንግልና ጸንሰሽ በድንግልና እንድትወልጂ ማድረግ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም ባላት ጊዜ እመቤታችን ድንግል ማርያም ለመልአኩ የእግዚአብሔር አገልጋዩ አለሁለት እንደቃልህ ይደረግልኝ አለችው ።

ይህንን ቃሏን ምክንያት በማድረግ ዋህድ ቃለ እግዚአብሔር በአጸብአ መንፈስ ቅዱስ በማኅፀንዋ ተቀረጸ ፤ ይህም የሆነው መጋቢት ፳፱ ቀን ነው ፤ ይህ ዕለት እግዚአብሔር አምላክ ሰዎችን ይቅር ለማለት የገባውን ቃል ኪዳን ለመፈጸም ሲል ከሰማየ ሰማያት ወርዶ በድንግል ማርያም ማኅጸን ያደረበት በመሆኑ ፤ ከጌታችን ከመድኃኒታችን ኢየ

ተከታዩን በ፳ኛው ገጽ ይመልከቱ



## ባለ ዕጣው ሐዋርያ

መራራ ሞትን ፊት ለፊት በመጋፈጥ መከራውንና ስደቱን እሥራቱንና ግርፋቱን እሳቱንና ስለቱን በመታገስ ሕይወታቸውን አሳልፈው እስከመስጠት ድረስ የክርስቶስን መስቀል ተሸክመው በግፍ አድራጊዎች አደባባይ እየተጓዙ በየሸንጎው እየተንገላቱ ቃለ ወንጌልን ያስተማሩ አሥራ ሁለቱ የጌታ ደቀ መዛሙርት ቅዱሳን ሐዋርያት ናቸው ።

አስቀድሞ ልበ አምላክ በሆነው ነቢዩ ዳዊት "እልቦ ነገር ወአልቦ ነቢብ ዘኢተሰምአ ቃሎሙ ውስተ ኩሉ ምድር ወጽአ ነገሮሙ ወእስከ አጽናፈ ዓለም በጽሐ ነቢቦሙ" ድምፃቸው ወደ ምድር ሁሉ ደረሰ ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ መዝ ፲፱፥፪—፭ ተብሎ የተነገረላቸው ቅዱሳን ሐዋርያት ከቅድስተ ቅዱሳን ንጽሕት ድ/ማርያም በነሣው ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር መመላለሱን በቅዱስ መስቀል ላይ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍሶ ዓለምን ማዳኑን ፤

ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ መነሣቱን በተነሣ በአርባ ቀኑ ወደ ሰማይ ወጥቶ በአባቱ ቀኝ መቀመጡን ዐይን በዐይን ዐይተዋል ዳግመኛ እንደሚመጣም ቃል በቃል አነጋግሮአቸዋል ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው ዐይን በዐይን ያዩትን ሐዋርያት "ሑሩ ወመሐሩ ውስተ ኵሉ አጽናፈ ዓለም ወስብኩ ወንጌለ ለዙሉ ፍጥረት" ወደ ዓለም ዳርቻ ሒዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ ማር ፲፮ ቁ ፲፭—፲፮ ብሎ በማይሻር ትእዛዙ በማይታበል ቃሉ በሰጣቸው አምላካዊ ትእዛዝ መሠረት ይህን ዓለም ዕጣ በዕጣ ተከፋፍለው የወንጌልን ቃል እስከ ዓለም ዳርቻ አዳርሰዋል ።

ከእነዚህም ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ በአስቆሮቱ በይሁዳ እግር የተተካው በሐዋርያት ሥራ ምዕ ፤ ፩ ፤ ቁ ፤ ፲፭—፳፮ እንደ ተጻፈው ቁጥሩ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት የነበረውና ጌታውንና መምህሩን አሳልፎ በመስጠቱ ከመዓርጉ በተለየው ከክብሩ በተዋረደው በአስቆሮቱ ይሁዳ ቦታ የተተካው ሐዋርያው ማትያስ ነው ።

ቦታው ምድረ በዳ ትሁን ሹመቱንም ሌላ ይውሰዳት ተብሎ በነቢዩ ዳዊት የተነገረውን ቃል በማውሳት ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ በተለየው በይሁዳ እግር ከአሥራ አንዱ ጋር ፲፪ኛ ሁኖ የሚቆጠር መተካት እንዳለበት ከገለጸ በኋላ "ወአቀሙ ክልዔተ ዮሴፍሃ ዘተሰምየ በርናባስ ዘይብልዎ ዮስጦስ ወማትያስሃ"

የጌታ የሞቱና የትንሣኤው ምሥክር የነበሩትን በርናባስና ማትያስን ሁለቱን አቀረቡአቸውና እጣ እንዲጣጣሉ ተደረገ "ወጸለዩ ሐዋርያት ወይቤሉ አንተ እግዚአ ማዕምረ ኵሉ ልብ አርኢአሐዶ እምእሉ ክልዔቱ ዘሐረይከ ዘይነሥእ ለመልእክተ ዛቲ ሢመት"

ሐዋርያተም የሁሉን ልብ የምታውቅ ጌታ ሆይ ይሁዳ ወደግዛ ሥፍራው ይሄድ ዘንድ በተዋት በዚህች አገልግሎተና ሐዋርያነት ሥፍራን እንዲቀበል የመረጥኸውን ከእነዚህ ከሁለቱ አንዱን ሹመው ብለው በእጣው ላይ ጸለዩ" ወወጽአ እፃ ዲበ ርእሰ ማትያስ ወተኆለቈ ምስለ አሠርቱ ወአሐዱ ሐዋርያት" እጣውም ለማትያስ ወጣ ከአሥራ አንዱ ጋርም አብሮ ፲፪ኛ ሁኖ ተቆጠረ ይህንም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በትርጓሜያቸው ሲአትቱ "ለማትያስ እጣው ወጣበት ቢል መከራ የሚቀበልበት ነውና ዕጣው ወጣለት ቢል ክብር የሚአገኝበት ነውና" በማለት ይተረጉሙታል ።

ሐዋርያው ቅዱስ ማትያስ ከአሥራ አንዱ ጋር ፲፪ኛ ሁኖ ከተቆጠረ በኋላ ስለሐዋርያዊ አገልግሎቱ መጋቢት ፰ ቀን የሚነበበው መጽሐፈ ስንክሣር እንደሚገለጸው ቅዱስ ማትያስ በእጣ በደረሰችው ወደ ሀገር በላዕተ ሰብእ ሂዶ ወንጌልን በሚአስተምርበት ጊዜ አረማውያን ሐዋርያው ማትያስን ዐይኑን አውጥተው ጥርሱን አውልቀው እስር ቤት አገቡት ።

ቅዱስ ማትያስ በእስር ቤት ሁኖ ሣር እየ ተመገበ ሳለ ከእግዚአብሔር ቅዱስ እንድርያስ ወደ ማትያስ ተልኮ ሂዶ ከእስር ቤት ከአወጣው በኋላ የሐዋርያው ማትያስ ዐይኖቹም ጥርሶቹም በተአምራት ተመልሰዋል እንደነበሩም ሁነዋል ።

በኋላም ማትያስ ከነበረበት እስር ቤት ከፍተኛ ማዕበል (ውኃ) ተነሥቶ አረ ማውያንን ሊአሰጥማቸው በመቃረቡ ወደ እግዚአብሔር እንዲጸልይላቸው ማትያስንና እንድርያስን አረማውያን ለመኑአቸው ሐዋርያትም ስለአረማውያን ወደ ጌታ በአቀረቡት ጸሎት ከእስር ቤቱ የተነሣው የውሃ ማዕበል ቆመ ፤ ተቋረጠ )

በዚህም ምክንያት በሐዋርያት ትምህርት አምነው በጌታ ስም ተጠመቁ ከዚህ በኋላ ሐዋርያው ማትያስ የእስያ ክፍል ወደ ሆነችው ወደ ሶርያ ሂዶ በደማስቆ ወንጌልን ሲያስተምር አረማውያን በብረት አልጋ ላይ አስቀምጠው በሥር እሳት አንድደው ሊአቃጥሉት ቢሞክሩ የእሳቱ ነበልባል ሳያቃጥለው ቀርቷል በዚህም ገቢረ ተአምር ከአሕዛብ ብዙዎች በጌታ ስም አምነው ተጠምቀዋል ።

ተከታዩን በ፱ኛው ገጽ ይመልከቱ

## ቃል ሥጋ ኮነ

ከ፮ኛው ገጽ የዞረ

ኢየሱስ ክርስቶስ ዘጠኝ ዓበይት በዓላት አንደኛውና ታላቁነው ስለዚህም ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በየዓመቱ በታላቅ መንፈሳዊ ሥርዓት ታከብረዋለች ።

መጋቢት ፳፱ ቀን የሚነበበውም ስንክሣር የበዓሉን ታላቅነት ሲገልጽ «ዝንቱ ዕለት በኩረ በዓላት ውእቱ ወቦቱ ኮነ ጥንተ መድኃኒተ ዓለም » ይህ ዕለት ከበዓላቱ ሁሉ የላቀና የከበረ ነው የዓለሙ የድኅነት መሠረት የተወጠነበት ነውና ይላል ስለዚህ በዓሉን አከብረን ከእግዚአብሔር አምላካችን ክብርን ለመቀዳጀት ያብቃን ።

ሊቀ ኅሩያን ልሣኑ በዛብኅ



www.ethiopianorthodox.org

# ትእምርተ መስቀል

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዓመት ሁለት ጊዜ የሚከበሩ የመስቀል በዓላት አሉአት ። ይኸውም አንደኛው መስከረም ፲፯ ቀን የሚከበረው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ መጋቢት ፲ ቀን የሚውለው ነው ።

እነዚህ ቀኖች ስለመስቀል በዓል አከባበር የሚገልጽ ታሪክ አላቸው ዓላማውም ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ነው ።

አይሁድ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል በምቀኝነት ተነሳስተው በአንድ አሳቻ ቦታ ለብዙ ምእት ዓመታት ቀብረውት ቆይተዋል ። በዚህ ምክንያትም ንግሥት እሌኒ ከተቀበረበት ፈልጋ ቆፍራ ለማውጣት አሰበች ፤ ለልጅዋ ለቆስጠንጢና ስም አማከረች ። ቆስጠንጢኖስም በሀሳብዋ ተስማማላት ።

ዕሌኒ ሀሳብዋን ሁሉ እግዚአብሔር እንዲያከናውንላት አስቀድማ ሱባኤ ገባች ፤ ጸሎትና ምሕላ ያዘች ። ከዚህ በኋላም እግዚአብሔር ልመናዋን ሰማት ደመራ አስደምራ በእሳት ለኮሰችው ። ጢሱ መስቀሉ ከአለበት ሄዶ ሦስት ጊዜ ሰገደ በዚሁ ጊዜ እሌኒ መስቀሉ በእርግጥ ከዚህ ተራራ መሰል ውስጥ መሆን አለበት ብላ መስከረም ፲፯ ቀን ቁፋር አስጀመረች ። በዚሁ ምክንያትም የመስቀል ደመራ በዓል በየዓመቱ መስከረም ፲፯ ቀን ሲከበር ይኖራል ።

የመጋቢት ፲ ቀን በዓለ መስቀል ታሪክ ደግሞ ከመስከረም ፲፯ ቀን ጀምሮ መስቀሉን ፍለጋ ሲቆፈር ቆይቶ በዚሁ ዕለት በመገኘቱ ቤተ ክርስቲያን ታከብረዋለች ፤ መስቀሉ ተቆፍሮ እንደወጣም በትክክል የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ለማወቅ ብዙ ዓይነ ሥውራን ሐንካሳን ፤ መፃጉዓን ፤ ድውያንና ልዩ ልዩ ደዌ ያላቸው ሁሉ እየመጡ መስቀሉን ሲዳስሱት ተፈውሰዋል ። ተአምራቱንም ሲገልጽ በመታየቱ ክርስቲያኖች ሁሉ ይህን ታሪካዊ ቀን ሲያከብሩት ይኖራሉ ።

ይህ መስቀል ከከርሠ ምድር ወጥቶ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ገብቶ በክብር እንዲቆይ ተደርጓል ። በኋላ ግን ግማደ መስቀሉ በአፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል ። በደብረ ከርቤ ግሸን ማርያምም በክብር ተቀምጦ ይገኛል ።

ሐዋርያው ጳውሎስ "በእርሱም አማካይነት በሰማይም ሆነ በምድር ያሉትን ሁሉ ከራሱ ጋር አስታረቀ በመስቀሉ በአፈሰሰው ደሙም ሰላምን አደረገ ፣ ፩ኛ/ቆር ፣ ፩ ፣ ፲፰ ።) ብሎአል።

በዓለም ብዙ የተለያዩ እምነቶች አሉ ። ከነዚህም የክርስትና እምነት አንዱ ነው ። ይሁን እንጂ በክርስትና እምነት ተከታዮች መካከልም ቢሆን ስለ መስቀሉ የተለያዩ አመለካከት ያላቸው አሉ ። በዚህ ምክንያትም ቅዱስ ጳውሎስ "የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉ ሞኝነት ፣ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው ። ብሎአል (፩ኛ ፣ ቆሮ ፣ ፲ ፣ ፲፱ ።)

ሰዎች አጥፊያቸው ማን እንደሆነና ጥፋታቸው ከምን ላይ እንደሆነ ቢያውቁና ከጥፋታቸው ቢመለሱ ኖር ከአምላክ ጋር ባልተጣሉ ፣ ከእግዚአብሔር ልጅነትም ባልወጡ ነበር ። የሰዎችን ደህንነት የማይወድ ዲያብሎስ ሰዎችን ሁል ጊዜ እግዚአብሔር የሚጠላውን ነገር መልካምና ትክክል በማስመሰል እያሳሳተ ከእውነተኛ መንገድ ሲያወጣቸው ይኖራል ።

ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "መስቀሌን ያልተሸከመ የኔ ደቀ መዝሙር ሊሆን አይችልም" ይላል ። ይህ አምላካዊ ቃል ሰዎች እንደፈለጉት ይተረጉሙታል ። እኛ ግን መስቀል የክርስትና እምነታችን አርማ ወይም ምልክት ነው ፤ ጠላታችን ሰይጣንም በመስቀል ስናማትብበት እንደጢስ ተና ፣ እንደትቢያ በኖ ይጠፋልና ። በመሆኑም በመስቀል እንመካለን እንታመናለን ።

መስቀል ከክርስቶስ ልደት በፊት የውርደትና የሐፍረት ምልክት ነበር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደሙን ካፈሰሰበት ጊዜ ወዲህ ግን የኃጢአት መደምሰሻ ፣ የመንግሥት ሰማያት መውረሻ የምእመናን ጋሻ ፣ የሕሙማን መፈወሻ ስለሆነ አርማችን ምልክታችን ፣ ተስፋችንና አለኝታችን ነው ።

ስለዚህም ካህናት መስቀሉን ተሸክመው ያስተምሩበታል ምእመናንም በምልክትነቱ ይጠቀሙበታል በማመናቸውም በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ ያገኙበታል ።

መስቀል እንዲህ በግልጽ ከመያዙ ወይም ከመደረጉ በፊት እውነተኛ ክርስቲያኖች አሰቃቂ መከራ ተቀብለውበታል ። እያንዳንዱ ካህን መስቀል እንዲይዝ እያንዳንዱ ምእመን በልብሱ ባንገቱ በሰውነቱ የመስቀል ምልክት የሚያደርገው ያለምክንያት ወይም ለጌጥ አይደለም ። ክርስቶስን ለመከተል በግብሩም ለመምሰል ነው ።

ሐዋርያው እንዳለውም የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉ ሞኝነት ለኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው ። መስቀል ኃይላችን ፣ መስቀል ጽንዓችን ፣ መስቀል ቤዛችን ፣ መስቀል መድኃኒተ ነፍሳችን ስለሆነ እንደሌሎቹ መስቀል መከራ ነው ፤ መስቀል በልብ ነው እያሉ ከሚያፈዙ ይልቅ መከራውን ውርደቱን ፣ ንቀቱን ከልብ ተቀብለን በትዕግሥት ጸንተን በተግባር ገልጸን ማሳየት አለብን ያለ መከራ ፀጋ እግዚአብሔር አይገኝምና ።

ሊ/ ትጉሃን ገ/ ክርስቶስ ኃ/ማርያም



# የቅዱስነታቸው ሐዋርያዊ ጉብኝት

## ጎጃም

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከጥር ፳፫-፳፰ ፲፱፻፺፯ ዓ/ም በምሥራቅና በምዕራብ ጎጃም ፤ በደብረ ማርቆስ ፤ በቢቸና በቆላ ደጋ ዳሞት በቡሬ በዳንግላ በመተከልና በባህር ዳር የሚገኙትን ታላላቅ ገዳማትና አድባራት ተዘዋውረው ጎብኝተዋል ። ለካህናቱና ለምእመናን አስፈላጊውን ትምህርትና አባታዊ ቡራኬ ሰጥተዋል ።

ቅዱስነታቸው ከጎበኟቸው ጥንታውያን ገዳማትና አድባራት መካከል ደብረ ማርቆስ ደብረ ኤልያስ ፤ ደብረ ድማህ ጊዮርጊስ ፤ ደብረ ወርቅ ማርያም ፤ መርጡለ ማርያም ፤ ቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ሞጣን ጊዮርጊስ የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል ።

በተለይ በጣና ሐይቅ ዳጋ እስጢፋኖስና ናርጋ ሥላሴ የሚባሉትን ጥንታውያንና ታሪካውያን ገዳማት ተዘዋውረው በመጎብኘት ትምህርትና ቡራኬ ከሰጡ በኋላ በጸሎትና በቅርስ ጥበቃ ለሚገኙ መናንያን የገንዘብ ርዳታ አድርገዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በዚሁ ሐዋርያዊ ጉብኝታቸው በደብረ ማርቆስ ፤ በሞጣ በደብረ ወርቅ በመርጡለ ማርያም በደንበጫ ቅዱስ ሚካኤል በገዳመ አስቴጥስ በአባገሪማ የሴቶች ደናግል ገዳም የኢ-ኦ- ተ-ቤ-ክ- የዘረጋቻቸውን የቤተሰብና ሕብረተሰብ የልማት እንቅስቃሴዎች ያስገኙትን ውጤት በመመልከት አስፈላጊውን ማበረታቻና መመሪያ ሰጥተዋል ።

ቅዱስነታቸው ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር በመሆን ተዘዋውረው በጎበኟቸው ታላላቅ አድባራትና ገዳማት ሁሉ ካህናትና ምእመናን እንዲሁም የየገዳማቱ መናንያን አበው በከፍተኛ ዝግጅትና በታላቅ መንፈሳዊ ሥርዓት አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

## ወለጋ ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የካቲት ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም ወለጋ ነቀምት ከተማ ሲገቡ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሕዝበ ክርስቲያንና ካህናት ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

ቅዱስነታቸው በነቀምት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው ለ፲ ደቂቃ ያህል የሀሊና ጸሎት ካደረሱ በኋላ የተዘጋጀላቸውን የክብር ሥፍራ እንደያዙ ለሕዝበ ክርስቲያን ባስበተላለፉት ቃለ ምእዳን የወለጋ ሕዝበ ክርስቲያን በክርስቲያናዊ ፍቅር ባደረገላቸው አቀባበል ከልብ የተደሰቱና ጥልቅ የሆነ ክርስቲያናዊ ስሜቱን የተረዱ መሆኑን በመግለጽ ሀገራችን ኢትዮጵያ ከሁሉ አስቀድማ በራሷ ፍላጎት ህገ ኦሪትን የተቀበለች ከመሆኗም በላይ የክርስትና ሃይማኖትንም የተቀበለችው ሌሎች ዓለማት ከመቀበላቸው አስቀድሞ መሆኑን ገልጸው ይህችን የእምነትናየታሪክየትምህርትና የቅርስ መሠረት የሆነችውን ባለውለታ ቤተ ክርስቲያን ሕዝቡ ውለታዋን አውቆ ፤ ጥቅም የእውነተኛ ሃይማኖት ባሕርይ ስላልሆነ በልዩ ልዩ ሃይማኖቶች እንዳትቦረቦር እንክብካቤ እንዲያደርጉላት አባታዊ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በዚሁ ሀገረ ስብከት እየተዘዋወሩ በጎበኙበት ወቅት ለብዙ አብያተ ክርስቲያናት ማሠሪያና ለሕግ እሥረኞች የገንዘብ ርዳታ ለግሰዋል ። ቅዱስነታቸው የወለጋ ሀገረ ስብከት ጉብኝታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ በአምቦ ሀገረ ሕይወት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው አቀባበል ለአደረጉላቸው ካህናትና ምእመናን ጥንታዊትና ብሔራዊት የሆነችውን የተዋሕዶ ሃይማኖት እንዲጠብቁና እንዲያስጠብቁ በማስገንዘብ ትምህርትና ቡራኬ ሰጥተዋቸዋል ።

### ባለዕጣው . . .

ከ፮ኛው ገጽ የዞረ

በመጨረሻም ሐዋርያው ቅዱስ ማትያስ በዚያው በሶርያ ወንጌልን ሲአስተምር ከኖረ በኋላ በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ መጋቢት ፰ ቀን እንዳረፈ ቅዱሳት መጻሕፍት ይናገራሉ

ሐዋርያው ቅዱስ ማትያስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የክርስቶስን መስቀል ተሸክሞ በአረማውያን ይደርስበት የነበረውን መከራ ሁሉ በመታገስ የወንጌልን ቃል በማስተማሩ ከአረማውያን ወገን ብዙዎች ከኃጢአት ወደ ሥርየት ከጨለማ ወደ ወንጌል ብርሃን ተመልሰዋል ።

በክርስቶስ ተመሥርታ በሐዋርያት ትምህርት ጸንታ ፫፻፲፰ቱ አበው ሊቃውንት በወሰኑት ቀኖና የምትመራው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየ ዓመቱ መጋቢት ፰ ቀን የሐዋርያው ቅዱስ ማትያስን መታሰቢያ ታከብራለች ።

የቅዱሳን ሐዋርያት ትዕግሥት የቅዱስ ማትያስ ጸጋና በረከት ከእኛ ከክርስቲያኖች ጋር ለዘለዓለም ይኑር አሜን ።

መሪጌታ ኤፍሬም በየነ



www.ethiopianorthodox.org

## የሰበካ ጉባኤ ዓላማና ተግባር

በዘመነ ኦሪት መንፈሳዊ አገልግሎት ይካሄድ የነበረው ምእመናኑ ከገንዘባቸው፣ከአዝመራቸውና ከጥሪታቸው በሚሰጡት አሥራት ነበር ።

አሥራት ማለት ከማንኛውም ገቢ ከአሥር አንድ ለቤተ እግዚአብሔር የሚሰጥ ክፍያ ማለት ነው ይህም የእያንዳንዱ ምእመን ሃይማኖታዊ ግዴታ ነበር ።

ሕገ ኦሪት ከመሰጠቱ በፊት አብርሃም ልእግዚአ ብሔር ካህን ለመልከ ጼዴቅ ከገንዘቡ ከእንስሳቱ ሁሉ ከአሥር አንድ እንደሰጠ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎአል ። (ዘፍጥ ፣ ፲፬፣፲፯—፳፬ ከቀደምት አበው አንዱ የሆነው ያዕቆብም ከሰጠኸኝም ሁሉ ለአንተ ከአሥር አንድ እሰጣለሁ ብሎ እንደተናገረው ሁሉ በዘመነ ኦሪት የነበሩ አበው ከገንበዛቸው ሁሉ ከአሥር አንዱን ለቤተ እግዚአብሔር ሲሰጡ ኑረዋል (ዘፍ ፣ ፳፰ ፣ ፲፰—፳፪) ።

ሕገ ኦሪት ከተሰጠበትና የሌዊ ልጆች ለክህነት ሥራ ከተመረጡ ወዲህም እግዚአብሔር ለሊቀ ካህናቱ ለአሮን "የሌዊ ልጆች እነሆ በመገናኛው ድንኳን አገልግሎት ስለሚሰጡ እሥራኤልን አሥራት ርስት አድርጌ ሰጥቼሃለሁ" ሲል እንደተናገረው ተጽፏል (ዘኁልቁ ፲፰ ፣ ፳፩—፴፪ ።

እግዚአብሔር ሰውን ከመውደዱ የተነሣ አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮ በመስቀል ላይ በመሰዋት ሕይወቱን ሰጥቶለታል ። ከጨለማ ወደ ብርሃን ከሞት ወደ ሕይወት አሸጋግሮታል ሰው ምንም እንኳ ይህን ውለታ በስጦታ መመለስ ባይችል ከአለው ሁሉ ለመለገስ በደሙ የመሠረታትን ቤተ ክርስቲያን ማገልገል ይኖርበታል ።

ስለዚህ እያንዳንዱ ክርስቲያን በዚህ ዓለም ስለ ክርስቲያናዊ ሕይወቱ በምግባርና በፍሬ ትሩፋት እንዲበለጽግ ያስፈልጋል ። የአንድ ምእመን የእምነቱ መግለጫ ስነ ምግባርና ልዩ ልዩ ትሩፋት ነው ከሃይማኖታዊ ምግባሩ አንዱም የአሥራት አስተዋጽኦነው።ዘመነ ኦሪት አልፎ ዘመነ ወንጌል በተተካበት ወቅት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈሪሳውያን ስለግብር አከፋፈል ሊፈታተኑት በቀረቡ ጊዜ "የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር የቄሣርን ለቄሣር» ሲል የተናገረው ቃል ከዘመነ ኦሪት ጀምሮ ሲፈጸም የነበረውን የአሥራት አስተዋጽኦ አስፈላጊነት የሚያረጋግጥ ነው ። (ማቴ ፣ ምጽ፣ ፳፪ ፣ ፳፩) ።

ተከታዩን በ፲፬ኛው ገጽ ይመልከቱ

## የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ከ፮ኛው ገጽ የዞረ

፪ኛ/ ከአዳምና ከሔዋን ጀምሮ እስከ ሐዲስ ኪዳን መግቢያ የነበሩ የደጋግ አባቶችና እናቶች «አንድነት» ስትሆን

፫ኛ/ ሦስተኛይቱና የመጨረሻይቱ በክርስቶስ ፣ ደም የተመሠረተችው «የክርስቲያኖች አንድነት» «ናት ።

እኛ ኢትዮጵያውያን በነባሩ ቋንቋችን በግእዝ ቤተ ክርስቲያን የምንለውን ቃል የጽርዕ ቋንቋ ተናጋሪዎች ግሪኮች አቅሌስያ ይሉታል ። ፍችውም ጸውዕት ፣ ጓሪት ማለት ነው ፣ ከጌታ ልደት በፊት በ፪፻፹፬ ዓለም ብሉይ ኪዳንን ከእብራይስጥ ወደ ጽርዕ ቋንቋ የተረጐሙ ሰብአ ሊቃናትም «ካሃል» የሚለውን የእብራይስጥ ቃል «ኤቅሌሲያ» ብለው ተርጉመውታል ። ትክክለኛ ትርጉሙም የኅሩያን እግዚአብሔር የእሥራኤል ጉባኤ ወይም አንድነት ማለት ነው ። እምልኮታቸውን ለመፈጸም ፣ በዓላተ እግዚአብሔርን ለማክበር የሚሰበሰቡሕዝበ እሥራኤል ሁሉ ኢቅሌስያ (ጉባኤ) ይባሉ እንደነበር በኦሪት ዘኁልቍ እና በዘዳግም ም-፲ - ፫ ፤፱ ፦ የተጻፈውን ይመለከቷል ።

፮ኛ/ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ምንጮች ፦

የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ በዝርዝር ለማጥናት ፤ ለቤተ ክርስቲያን ታሪክ ምንጮች የሆኑትን ልዩ ልዩ መጻሕፍት መመልከትና መመርመር ያስፈልጋል ። እነሱንም በዝርዝር ለማመልከት ፤

፩ኛ/ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን

፪ኛ/ ጥንታውያን የቤተ ክርስቲያን አበው የጻፏቸው መጻሕፍት ፤

፫ኛ/ በየጊዜው ስለእምነትና ስለቀኖና ፤ እንዲሁም ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር የተደረጉት ጉባኤዎች የተወሰኑት ውሳኔዎች ፤ የተደነገጉት ሕጎች ፤

፬ኛ/ በየጊዜው በከርሠ ምድር የተገኙትና የሚገኙት የአርኪዎሎጂ / የጥንታውያን ነገሮች ምርመራ/ ውጤቶች (ቅርሶች) ፣ ናቸው ።

፮ኛ/ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አከፋፈል ፦

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በሦስት ክፍሎች ይከፈላል ።

አከፋፈሉም ፦ ፩ኛ/ ጌታ ቤተ ክርስቲያንን በሐዋርያት መሠረትነት ላይ ከመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ትልቁ ቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት ድረስ ማለትም እስከ ፫፻፳ ዓ/ም

፪ኛ/ ከትልቁ ቆስጠንጢኖስ ጀምሮ ቁስጥንጥንያ በቱርኮች እጅ እስከወደቀችበት ድረስ ማለት ከ፫፻፳-፩ሺ፬፻፶፳ ዓ/ም

፫ኛ/ ቁስጥንጥንያ በቱርኮች እጅ ከወደቀች በት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁንበት ዘመን ማለትም ከ፩ሺ፬፻፶፳- ፩ሺ፱፻፹፯ ዓ/ም መሆኑ ነው

ይቀጥላል

ሊቀ ካህናት ብርሃኑ ገ/ አማኑኤል
የትንሣኤ ማሳተሚያ ዲሬክተር



## ጥንታዊና ብዙኃዊ የኢትዮጵያ ትምህርት

ፊደል ማለት የቋንቋና የቃል የአነጋገር ሁሉ ምልክት ፣ ምሳሌ ፣ ወይም መግለጫ ፣ ማስታወቂያ ማለት ነው ። የሰው ሁሉ መልክ በጥሩ ሥዕል ፣ በፎቶ ግራፍ ፣ በቴሌቪዥን ፣ በመስተዋት ታይቶ ተለይቶ እንዲታወቅ የማይታየውም ሥውር ንባብ ፣ ረቂቅ አሳብ ፣ በቀለም ገዝፎ ፤ በወረቀት ተጽፎ በፊደል መልክ ታይቶ ተለይቶ ይታወቃል ።

በግዕዝ ቋንቋ ፈደለ ብሎ ጻፈ ፣ ቀጠረ ፣ ለየ ፣ መረጠ ስለሚል ፊደል የሚለው ዘር ከዚህ ይወለዳል ። ጽሕፈት ፣ ልዩ ፣ ምርጥ ማለት ነው ። ዐረቦች ሐርፍ፣ ዕብራውያን አት ይሉታል ። በተገናኝ ምልክት ማለት ነው (መዝገበ ቃላት ዘኪዳነ ወልድ ክፍሌ ገጽ ፳፯ ተመልከት )

ተከታዩን በ፲፫ኛው ገጽ ይመልከቱ

## የመጽሐፍ ቅዱስ ቀን በዓል . . .

ከ፫ተኛው ገጽ ዞረ

ለከተ መልእክትና መቀጫ በየተራ አስተላልፈዋል ። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች ያሬዳዊ መዝሙሮች፣



መንፈሳውያን ወጣቶች በበዓሉ ላይ ተገኝተው መዝሙር ሲያሰሙ

በሌሎችም ሌሎች መዝሙሮች ተዘምረዋል ።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በይፋ ከተቋቋመበት እ - ኤ - አ - ፲፱፻፳፮ ዓ/ም ጀምሮ ከኢት/ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከካቶሊክ ከሌሎችም የክርስትና እምነት ተከታዮች በተመረጡ አባላት ቦርድ ይተዳደራል ።

— ዓላማው ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ሰዎች በሚረዱት ቋንቋና ሊገዙ በሚችሉት አነስተኛ ዋጋ አዘጋጅቶ ማቅረብ ሲሆን እስከዛሬ በሰጠው መንፈሳዊ አገልግሎት ቅዱሳት መጻሕፍትን በልዩ ልዩ ቋንቋዎች እያስተረጐመ ማንበብ ለሚችሉ ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ የመ/ቅ ክፍሎችን በተለያዩ

ተከታዩን በ፩ኛው ገጽ ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

# ክርስቶስ

## ፍጹም

## አምላክ ነው

በዚህ ዓለም የሚሠራ ሥራ ሁሉ ቅደም ተከተል አለው ፤

ቅደም ተከተሉ ተጠብቆ ይሠራል ፤ በቅድሚያ ግን ከሥራው በፊት የሠራተኛ መኖር ወሳኝ ነው ። ሥራና መሥሪያ መሣሪያም ይከተላሉ ። ከዚያ በኋላ የሥራ ዝርዝር አውጥቶ ሠራተኛና ሥራ እያገናኘ ያሠራል ። ሥራም ቢበዛ በዓይነቱ በየዝርዝር ሥራው ልክ ሠራተኛ ይመድባል ።

እንግዲህ ይህ አመለካከት ወደጥንተ ተፈጥሮ መርቶ ያደርሰናል ። በመሠረቱ የዓለማት ሠራዒና መጋቢ እግዚአብሔር ከፍጥረት መፈጠር በፊት የነበረና ያለ ወደፊትም ፍጻሜ በሌለው ዘላለማዊነት የሚኖር እንደመሆኑ መጠን በቅድሚያ መሥሪያ ቦታ ሰማይና ምድርን ፤ መሣሪያ ፤ አራቱን ባሕርያት ፈጠረ «ዘፍ ም ፩ቁ- ፩ ቀጥሎ በተከታታይ ዕለታት ቀን ለይቶ ኽያ ሁለቱን ሥነ ፍጥረት አከናወነ ። የፍጥረቱ ክንውን እንደ ፈቃዱ ጥሩ መልክ ያለው ሆኖ ተገኘ» ዘፍ፩ ቁ ፴

ለዚህም ፍጥረቱ አስተናባሪ ስለ አስፈለገው «ሰውን በአርአያችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር» በማለት ሰውን ፈጠረ ። ዘፍ ም ፩ቁ ፳፮ እዚህ ላይ አትኩረን ልንመለከተው የሚገባ ትምህርት አለ ፤ እግዚአብሔር ስንል አብ ፤ ወልድ ፣ መንፈስ ቅዱስ ማለታችን ነው ። እግዚአብሔር ያንድነትም የሦስትነትም ስም ነውና ይኸውም በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ ባለው ይታወቃል ። እኔ ልፍጠር አንተ ፍጠር እርሱ ይፍጠር አላለም ። እን ፍጠር ብሎ ሦስትነቱን ነገረን ። በአርአያነ ብሎ ሲያበዛ» በአርዓያችን ብሎ አንድነቱን ነገረን ። አንሰሶበ እቤ እግዚአብሔር እብል በአንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ብሎአል ባስልዮስ ዘአ ንጾኪያ መልካሙና ክፉን ለማወቅ አዳም ከኛ እን ዳንዱ ሆነ ዘፍ ፩ ፣ ፳፪

አዳም ኮነ ከመ አሐዱ እምኔነ ይኸም ቃል ከሦስቱ አካላት አንዱ ወልድ አዳም ኮነ ከመ አሐዱ እምኔነ ኖሮ ኖሮ በኋላ ዘመን የአዳምን ሥጋና ነፍስ ተዋሕዶ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ መሆኑን ያሳያል የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ አምላክ የያዕቆብ አምላክ ነኝ ዘጸ ፫ - ቁ - ፯ ።

እኔ የአባትህ አምላክ ነኝ በማለት አንድነቱን ፤ በሦስቱ አባቶች ስም ልክ ሦስት ጊዜ አምላክ አምላክ አምላክ በማለት ደግሞ ሦስትነቱን ገለጸልን ። በአጠቃላይም ለደቀ መዛሙርቱ መመሪያ ሲሰጥ እንግዲህ ሒዱና አህዛብን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ የአዘዝኋችሁን ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችሁ ደቀ መዛሙርት አድርጓ ቸው ። ማቴ ፳፰ ቁ - ፲፱ በማለት የሦስቱን መጠሪያ ስማቸውን አንድ ባንድ ዘርዝሮ አስቀምጦታል ። ማመንም መጠመቅም ትክክለኛ የሚሆነው በሦስቱ ስም ሲያምኑና ሲጠመቁ ብቻ ነውና በሦስቱ ስም አምኖ ያልተጠመቀ ግን ይፈረድበታል እንጂ ዮሐ ፫ ፣ ፴፮ ማር-ም ፲፮ ፣ ፲፮ ተብሎአል እንጂ ሕይወት የለውም ። አምላክነቱን ማመን ይገባል ምን ጊዜም ወረደ ተወለደ እያለ ቅዱስ መጽሐፍ በየምዕራፉ የሚናገርለት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው ። ምክንያቱም ከሦስቱ አካላት አንዱ እግዚአብሔር ወልድ ነውና በዚህ መሠረት ነቢዩ ኤርምያስም ጌታ ኢየሱስ ከሰማይ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ እንደሚሆን ሳይሠውር በግልጥ ሳይደብቅ በማረጋገጥ ጽፎለታል ። እንዲህ ሲል ፤ ፈጣሪያችንን ባንድ ቃል አመስግኑት ፣ የሚያስነሣችሁ የአብ ልጅ ወልድንም አመስግኑት ። የዓለሙ ብርሃን የሚሆን የአብ ልጅ ኢየሱስም ይፈርድባችኋል ። እሱም ራሱ ሰው ሆኖ ወደዚህ ዓለም ይገባል ። እኔ ሰው ሆኖ ያየሁት ፤ ከባሕርይ አባቱም ወደዚህ ዓለም የተላከ ፤ ሰው ሁኖም ወደ ዚህ ዓለም የመጣ እርሱ አብሯቸው ይታይ ዘንድ ፤ ይገለጥላቸው ዘንድ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያትን ይመርጣል ። ለማስተማር ወደ ደብረ ዘይት ይወርዳል ። የተራበች ሰውነትንም ሁሉ ያጠግባል ። ጌታ ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም እንደሚመጣ ፤ ኤርምያስ የአምላክን ልጅ ነገር እንዲህ አድርጎ ተናገረ ተረፈ ኤር- ፲፩ቁ ፵፰ - ፶፰ ።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ኃይለ ቃሎች (ጥቅሶች) ከልደተ ክርስቶስ አስቀድሞ በነበሩት ነቢያት የተነገሩ ትንቢቶች ሲሆኑ ከፍጥረቱ ሁሉ በፊት ቅድመ ዓለም የነበረ ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ለአምላክ እናትነት በመንፈስ ቅዱስ ከተመረጠችው በቅድስና ከተጠበቀችው ከድንግል ማርያም ሥጋና ነፍስን ነሥቶ በመዋሐድ ሰው ሆነ እንጂ አምላክነት የሌለው ሰው አልሆነም ከእንግዲህ ወዲህም ሰው አይሆንም አምላካዊ ባሕርዩን ሳይለቅ ራሱን ዝቅ አድርጎ ወደ ዓለም መጥቶ በሥጋዊ አካል የተገለጠውና ስለበደላችን ራሱን ካሣ አድርጎ ክቡር ደሙን አፍሶ ያዳነን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአሁን በፊት ተወልዶአል ። ገና ወደፊት ይወርዳል ይወለዳል የሚሉም ሆነ ፤ ክርስቶስ ፍጡር ነው እንጂ አምላክ አይደለም አይወለድም የሚሉ የሰባል ዮስን ባሕል የሚከተሉ ሁሉ የሃይማኖት መንገድ የጠፋባቸው ስለሆነ ነቢዩ ኢሳይያስ በም - ፱ ቁ ፯ ላይ ሕጻን ተወልዶልናልና ወንድ

ተከታዩን በ፲፬ኛው ገጽ ይመልከቱ



# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

## በዓለም አቀፍ


ከአለፈው የቀጠለ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊትና ታሪካዊት ቤተ ክርስቲያን እንደመሆንዋ መጠን እናት ቤተ ክርስቲያን የሚለው ተጸውኦ ስም በዓለም አቀፍ ደረጃ የተለመደ አጠራር እየሆነ መጥቷል ። ይህ ሲባል ግን ለቃለ አጋኖ የገባ ስርዋፅ ወይም ሐረግ ያለመሆኑን እንዲታወቅ ያሻል ። ምክንያቱም የቀደምት ታሪክነትዋ እንደ አጉሊ መነጽር በዓለም አቀፍ መድረክ አጉልቶ በማሳየቱ ነው ።

በዓለም አቀፍ አጠራር የኦሪንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት አምስት ናቸው ።

፩/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
፪/ የእስክንድርያ (ኮፕቲክ) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን
፫/ የሶርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን
፬/ የአርመን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን
፭/ የሕንድ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን

ሲሆኑ እነዚህ አምስቱ አብያተ ክርስቲያናት ተመሳይ የእምነት መንገድ አላቸው ። በአምልኮተ እግ



የኢትዮጵያና የእስክንድርያ አብያተ ክርስቲያናት ሊቃነ ጳጳሳት በውይይት ላይ እንዳሉ

ስለዚህ መልእክተኞቿ በዓለም ዓቀፍ ስብሰባዎች ላይ በሚሳተፉበት ጊዜ ሁሉ ቤተ ክርስቲያናችን የተለየ ክብርና ሞገስ ፀጋ ያላት ቤተ ክርስቲያን መሆንዋ በከፍተኛ ደረጃ የታየ ስለሆነ ይህ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካውያን ወንድሞቻችን ጭምር መመኪያና አለኝታ ስለሆነ በዓለም አቀፍ መድረክ ያለን ትውውቅ የጋራችን ነው ቢባል ከእውነት የራቀ አይደለም ።

ዚአብሔር በኩል ከላይ ከተጠቀሱት አብያተ ክርስቲያናት መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት የለም ከቋንቋና ከአንዳንድ ጥቃቅን የውስጥ ሥርዓቶች በቀር የእምነት ልዩነት የለም ። በእስክንድርያ ኦርቶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንደ ጥንቱ የነበ

ተከታዩን በ፲፱ኛው ገጽ ይመልከቱ

# ጥንታዊና ብሔራዊ የኢትዮጵያ ትምህርት

ከ፲፩ኛው ገጽ የዞረ

ፊደልና ጽሕፈት ለአዳም ልጆች የተገለጡና የተሰጡ በአዳም ዕድሜ ነው ። ይኸውም በሰባተኛው መቶ ዓመተ ዓለም በሦስተኛው ትውልድ በሄኖስ ዘመን እንደሆነ ይነገራል ።

በሄኖስ ዘመን የነበሩ ሰዎች ዕንጨት ጠርበው ድንጋይ አለዝበው ብዙ ዓይነት ቀለም እየቀቡ ሸልመው አስጊጠው በሚያመልኩት በምስሉ ፈንታ በድንጋይና በዕንጨት ስሌዳ በእንስሳትምዐይነት ተቀርጾ ተጽፎ ተደጉሶ ታፍፎ ሁለመናው ገዝፎ የሚታይና የሚዳስስ መጽሐፋዊ ሕግ ያቆምላቸው ዘንድ ስለአሰበ ሄኖስን በራእይ እንደ ሙሴ ስቦ በባለሟልነት አቅርቦ ረቂቁን ሕግና ትእዛዝ አግዝፈው አጉልተው የሚያሳዩ የዐይን ልቡና መነጽሮች ፊደላትን ሰጠው። ፳፪ቱን አሌፋት በ፳፪ ስነ ፍጥረታት ምሳሌ በጸፍ

ተከታዩን በ፳፳ኛው ገጽ ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

## ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ነው

ከ፲፫ኛው ገጽ የዞረ

ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነቱም በጫንቃው ላይ
የሆነ ፣ ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ ፣ የዘለ
ዓለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል ያለ
ውን ተመልክተው ከልባቸው በማስገባት አምነው
አምላክነቱን ተቀብለውበመጨረሻዪቱ ቀን ሲመጣ
እናንተ ግን ከበጎቼ ወገን አይደላችሁምና አላው
ቃችሁም እንዳይባሉ ትክክለኛውን ትምህርት እና
ስተምራቸዋለን ቀናውን ምክር እንመክራቸዋለን
የህይወት ጉዳና እናሳያቸዋለን ብሎአልና ዮሐ -
፲ - ቁ - ፴፰

### የክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፣ ፍጹም ሰው መሆን ፣

ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ፣
ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ ፍጹም ሰው ፣ ፍጹም አምላክ
ሆነ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ሰው መሆኑም እንደ እን
ግዳ ደራሽ እንደ ውኃ ፈሳሽ በመሆን አይደለም ።
አስቀድሞ በዘመነ አበው በነበሩ ፣ በእነሄኖክ ፣
ኋላም በዘመነ መሳፍንት ፣ ቀጥሎም በዘመነ ነገ
ሥት በነበሩ ትቢንት አናገር ሱባኤ አስቆጥር ፣
አስጠንቶ ነው እንጂ ።

ከሰማየ ሰማያት ለመውረዱ ምን ትንቢት
አናገሯልን ቢባል «እግዚአብሔርም አለ ፣ የሕዝቡን
መከራ በእውነት አየሁ ፣ ጩኸታቸውንም ሰማሁ ።
ከጠላቶቻቸውም እጅ አድናቸው ዘንድ ወረድሁ»፣
ዘፀ ፫ ቁ ፰ ።

፩ኛ/ እንደ ዝናብ በታጨደ መስክ ላይ በም
ድር ላይ እንደሚንጠባጠብ ጠብታ ይወርዳል ፣
በዘመኑም ጽድቅ ያብባል መዝ ፸ ፩ ቁ ፮ ።

፪ኛ/ እስራኤልን እንደ መንጋ የምትመራ የእ
ስራኤል ጠባቂ ሆይ አድምጥ ፣ በኪሩቤል ላይ የም
ትቀመጥ ተገለጥ ኃይልህን አንሣእኛንም አጽናናን
አቤቱ መልሰን ፣ መዝ ፸፱/ ፹/ቁ ፩-፱ ።

### ከድንግል ለመወለዱ የተነገረ ትንቢት

እርሱ ራሱ ጌታ ምልክት ይሰጣችኋል ፣ እነሆ
ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ፣
ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች ፣ኢሳ፯ ቁ/
፲፬ «እንግዲህ የመዳን ምልክት ያደረገላቸው ከሰው
ልማድ የራቀችውን የሰው ልማድ ዘርና ሩካቤ ያላ
ገኛት ፣ በቅድስና የተጠበቀችውን ለአምላክ እና
ትነት በመንፈስ ቅዱስ የተመረጠችው ድንግል
ማርያምን ነው ፣ ምልክትነቷም ሰው የሆነው አም
ላክ አማኑኤልን በድንግልና ጸንሳ በድንግልና መው
ለዷ ነው ። እንዲሁም ጌታ እግዚአብሔር ከፊት
ሁሉ እንባን ያብሳል ። የሕዝብንም ስድብ ከምድር
ሁሉ ያስወግዳል ፣ እግዚአብሔር ተናግሮአልና ፣
በዚያም ቀን እነሆ አምላካችን ይህ ነው ተስፋ
አድርገነዋል ያድነንማል እግዚአብሔር ይህ ነው ፣
ጠብቀነዋል በማዳኑም ደስ ይለናል ፣ ሐሴትም እና
ደረጋለን ፣ ኢሳ ፳፭ ቁ - ፰ - ፱» እነሆ ኢሳይያስ
ተስፋ አድርገነዋልና ያድነናል በመዳኑም ደስ ይለ
ናል ያለው ፣ ወገኖቹን ከኃጢአታቸው ፍዳ ያድ
ናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ብለህ ትጠራዋለህ ማቴ -
፩ቁ ፳፩» ብሎ መልአኩ ቅ/ገብርኤል አዳኝነቱን
በይፋ የመሰከረለት ጌታችን አምላካችንና መድኃ
ኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ማወቅ መረዳ
ትና በፍጹም ልብ አምላክነቱን ማመን ይገባል።

ብፁዕ አቡነ አብርሃም የስብከተ ወንጌልና ሐዋ
ርያዊ ተልእኮ መምሪያ የበላይ ጠባቂ ሊቀ ጳጳስ

## የሰ በ ካ ጉ ባ ኤ - - - -

ከ፲ኛው ገጽ የዞረ

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በሁለተኛው የቆ
ሮንቶስ መልእክቱ» ይህንም እላለሁ በጥቂት የሚ
ዘራ በጥቂት ያጭዳል በበረከትም የሚዘራ በበረ
ከ ት ይ ሰ በ ስ ባ ል ። እ ግ ዚ አ ብ ሔ ር
በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ
እንዳሰበ ይስጥ በኀዘን ወይም በግድ አይደለም »
ሲል ያስገነዘበው ቃል እያንዳንዱ ምእመን ለቤተ
ክርስቲያን የሚገባውን አስተዋጽኦ መለገስ እንዳ
ለበት ያረጋግጣል ፣ (፪ኛ ፣ ቆሮ ፱፣፯—፯

ኢትዮጵያውያን ምእመናን ሕገ ኦሪት በሀገራችን
ከገባበት ጊዜ ጀምሮ የኦሪቱን ሕግ በመከተል የሚ
ገባውን አሥራት በኩራት ለቤተ እግዚአብሔር ሲያ
ቀርቡ እንደኖሩ አሁንም በተግባር የሚታይ ሐቅ
ነው ።

ይሁን እንጂ የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ አገል
ግሎት በይበልጥ የተሟላ ለማድረግ ይቻል ዘንድ
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ቅዱስ ሲኖዶስ ያዘጋጀው "ቃለዓዋዲ" የቤተ ክርስ
ቲያን መተዳደሪያ ደንብ በሥራ ላይ ከዋለ ዓመታት
አልፈዋል ።

በዚሁ ደንብ መሠረትም በየአጥቢያ ቤተ ክር
ስቲያን ክልል የሚገኙ ምእመናንን በሰበካ ጉባኤ
ለማደራጀት ቃለ አዋዲ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ያደ
ረገው ጥረትና ያስገኘው ውጤት በቀላሉ የሚገ
መት አይደለም ።

ተከታዩን በ፲፭ኛው ገጽ ይመልከቱ



## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

### ከመምህር ሀ/ማርያም ተድላ

#### ለገነት የምትቀርብ አገር

ወተከለ እግዚአብሔር አምላክ ውስተ ኤዶም
ገነተ መንገለ ጽባሕ «እግዘአብሔር አምላክም
በኤዶም ምሥራቅ በኩል ገነትን ተከለ / የአታክ
ልትቦታን አዘጋጀ/ የፈጠረውንም ሰው ከዚያ አኖ
ረው» ዘፍ ፪-፰ ።

በመጀመርያ እኛ ኢትዮጵያውያን በየት አካ
ባቢ መኖራችንን ከመመርመራችን በፊት እስቲ
«ምድር ፣ ገነት» የተባሉትን ሁለት ቃላት እን
መልከት ፩ «ምድር»እንስሳት አራዊት የሚራቡባት ፣
ዕጽዋት የሚያብቡባትና የሚያፈሩባት ፣ ሕይወ
ትና ሞት የሚፈራረቁባት አደባባይ መሆኗን እያ
የን ነው ።

የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያስተምረን ፣
«የባሕር ዓሣዎችን ፣ የሰማይ ወፎችን ፣ የምድር
አራዊቶችን ፣ ራስዋን ምድርንና በምድር የሚንቀ
ሳቀሰውን ፍጥረት ሁሉ የሚገዛ ሰው በመልካችን
እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር» በማለት እግዚአብ
ሔር ሰውን በአምሳሉ ከምድር አፈር በዚህችው
ምድር የፈጠረው መሆኑን እንረዳለን ዘፍ- ፩-፳፮ ።
ቀጥሎም «ወገብሮ ለእጓለ እመሕያው በአምሳለ
እግዚአብሔር ፣ ተባዕተ ወአንስተ ገብሮሙ» ሰውን
በእግዚአብሔር አምሳል ፈጠረው» ካለ በኋላ ሴትና
ወንድ አድርጎ መፍጠሩን ፣ በዚህም አያይዞ «ባረ
ካቸው ፣ ብዙ ፣ ተባዙ ፣ ምድርንም ምሉአት ፣ ግዙ
አትም» በማለት ምድርን የሚንቀሳቀሰውን ፍጥ
ረት ሁሉ እንዲገዙ ሥልጣን የሰጣቸው መሆኑን
እንገነዘባለን ። ዘፍ - ፪ - ፳፯—፴፩ ።

ምድርንና በምድር የሚንቀሳቀሰውን ፍጥረት
ሁሉ እንዲገዙ ለመብል መልካም የሆነውን እንዲ
በሉ ፣ ለዓይን ደስ በሚያሰኘውም እንዲደሰቱ ሲፈቅ
ድላቸው የሚታገዱበት ድንበርና ወሰን አልከለለባ
ቸውም ነበር ።

፪/ «ገነት» ከላይ በመጀመርያው መሥመር
እንዳየነው ልዑል እግዚአብሔር በኤዶም ምሥ
ራቅ በኩል ገነትን ተከለ ፣ (የአታክልት ቦታን አዘ
ጋጀ) ገነት ማለት ለዓይን ደስ የሚያሰኙና ለመብ
ላትም መልካም የሆነው ሁሉ የሚመረትበት ፣ ሁል
ጊዜ ለምለም የሆነ ቦታ ነው ፣ ስለዚህ እግዚአብ
ሔር አምላክ ከገነቱ ክልል ከኤዶም ውሀን አመ
ነጨ ፣ ውሀውም በአራት የተከፈለ ነበር ። እነዚ
ህም አራት አፍላጋት በሚከተሉት ስሞች ይታወ
ቃሉ ።

የአንደኛው ወንዝ ስም ኤፌሶን ፣
የሁለተኛው » » ግዮን( ይህ ወንዝኢት
ዮጵያን የሚከብ ነው
ሦስተኛው » » ጤግሮስ
የአራተኛው » » ኤፍራጥስ ይባላሉ ዘፍ
፪-፲-፲፯

በዚህች ገነት ውስጥ ለዓይን የሚያስደስቱ ለምግብ
የሚበጁ አታክልትን አበቀለ ፣ በዚህች ገነት መካ
ካከል ሁለት የተለያዩ የሕይወትና የሞት ዛፎችን
አዘጋጀ ። አዳምንም ከሔዋን ጋር የዚህች ገነት
ባለቤት አድርጎ ሾመውና በዚያች ውስጥ እኖረው
እንዲጠብቋትና እንዲንከባከባትም አዘዘው ዘፍ ፪
፲፭ ። በገነት ውስጥ ያለውን ሁሉ ብላ ጠጣ ግዛ
ንዳ ፣ በገነት ውስጥ ያለችውን ፣ ክፋንና ደጉን የም
ታስታውቀውን ግን እንዳትበላ ፣ እንዳትነካትም ፣
ከሷ በበላህ ጊዜ የሞት ሞት ትሞታለህ» በማለት
አስጠንቅቆት ነበር ። ዘፍ - ፪ - ፲፮ - ፲፯ ።

እግዚአብሔር አምላክ አዳምን በፈጠረው ፍጥ
ረት ሁሉ ላይ ሊያሠለጥነው «ክፋንና በጎን የምታ
ስታውቅ»የተባለችውን ዕፅ ለምን ከለከለው? ማንም
ሰው ሊያነሣው የሚችል ጥያቄ ነው ። በመሠረቱ
«ወኃቤ ዘእንበለ ክልአት» ምንም ምን ሳይከለክል
ሁሉን በለጋስነት የሚሰጥ አምላክ ሁሉን ነገር
ከሃሊነቱ ካልነበረበት አምጥቶ የሰጠው ሲሆን በዚች
ዕፅ ሌላ ምክንያት ኑሮት ሳይሆን ፣ አምላክነቱን
ለመግለጽ በፈጣሪና በፍጡር መካከል የአዛዥነትና
የታዛዥነት ሥርዓት እንዲኖር የሠራው ሕግ እንደ
ሆነ ነው የሚታየው ። ዘፀ - ፳ - ፩—፲፰ ፣ ዘሌ -
፲፱-፲፰ ፣

አሁንም ማንኛውንም አንባቢ ለማስገንዘብ
የምወደው እነዚህ ሁለት ዕፅዋት / ዕፀ ሕይወትና
ክፋንና በጎን ለይታ የምታስታውቀው ዛፍ/ አሁን
ባለንበት ገነት መኖራቸውን ነው ። እነዚህም ፩-
በጎን ለይታ የምታስታውቅ ዕፅ «ኢታምልክ ባዕደ
አምላክ ዘእንበሌየ» ከሚለው አንሥቶ «አፍቅር
ቢጽከ ከመ ነፍስከ» እስከሚለው ዐሥር ቅርንጫ
ፎች ያሉትና ስድስት ቃላተ ወንጌል ፍሬያት የሚ
ገኙበት መሆኑን ነው ፣ ማቴ ፣ ፳ ፣ ፲፩—፵፰ ።

፪/ ዕፀ ሕይወት የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና
ደም ሲሆን ኢታመልክ የተባለው ትእዛዝ ከአሥሩ
ቃላተ ኦሪትና ከስድስቱ ቃላተ ወንጌል እንድንጠ
ብቀው የተሰጠን ትእዛዝ ስለሆነ ሁላችንም የአ
ዳም ልጆች የመጠበቅ ግዴታ አለብን ። ትእዛዙንስ
ጠብቀን ፣ ዕፀ ሕይወት የተባለውን የጌታ ሥጋና
ደም ተቀብለን የዘለዓለምን ሕይወት መውረስ አል
ተነፈግንም ከፈለነ ንብለዕ እምእፀ ሕይወት ዘው
እቱ ሥጋሁ ለክርስቶስ ፣ ወደሙ ክቡር በእንተ ፍቅረ
ዚእነ - - - ተብሏልና ወደ ጥንቱ ታሪካችን ስንመለስ
አዳምና ሔዋን በዚያች በገነት ሳሉ ፍጥረታት ሁሉ
ይገዙላቸው ነበር ፣ ረኃብ ጥማት እርዛትና የመሳሰሉ
ችግሮችም አልነበሩባቸውም ነበር ። እንደመላእክት
ሕያዋን ሁነው እንዲኖሩ እንጂ ለሞት ባለመፈጠራ
ቸውም ሕማምና ሞት አልነበረባቸውም ታዲያ
በዚህ ሕይወት መኖራቸውን የተመለከተ ከይሲ
ዲያብሎስ በቅንዓት ጦር ተወጋ፤ቈስለ ። በተንኮልም
ጠያቂ ዘመድ መስሎ ወደ ሔዋን ጉራ አለ ። በውኑ

ተከታዩን በ፲፰ኛው ገጽ ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ድርሻ

## የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች ምስክርነት

ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል መስማትና መገር በቃሉ የታዘዘውንም በተግባር ላይ ማዋል የሚገባ መሆኑን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታይ የሆነ ሁሉ ያውቀዋል ።

በተለይም በቤተ ክርስቲያኒቱ የሰንበት ት/ቤት ከተመሠረተ ወዲህ ወጣቶች የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት በሚገባ እየተማሩ ክርስቲያናዊ ሕይወትም መሆን እንዳለበት ገና ከሕጻንነታቸው ጀምረው እየተማሩ ማደጋቸው ጠቃሚ ሆኖ ተገኝቷል ።

መንፈሳውያን ወጣቶች በእግዚአብሔር ቃል የታነጹ ከመሆናቸው የተነሣ ተኩላ ነጣቂ ቢመጣ የእግዚአብሔርን ቃል በትር አድርገው ተከላክለው ይመልሱታል ።

ይህን ያላወቁ አግሌቃውያን ወጣቶች ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ወጣቶች መካከል ያውም የሰንበተ ት/ቤት አባላት የሆኑትን ለመስበክ አስበው ቀስ በማለት እንደበታቸውን ለስለስ አድርገው ጠጋ ይላሉ ።

ቦታው ቀድሞ ልዑል መኩንን አሁን አዲስ ከተማ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚባለው ነው ። ጊዜው የተምህርት ጊዜ ሆኖ በዕረፍት ሰዓታቸው ከክፍል በመውጣት ከአንድ ጥላ ሥር ቁጭ ብለው ወደ ኳስ ሜዳው ዓይናቸውን ወርወር በማድረግ አንዳንድ ወጣቶች ከኳስ ጋር ሲታገሉ አንዳንድ ወጣቶች ደግሞ አንዱ ሌላውን ሮጦ ለመቅደም የሚያደርጉትን እሽቅድምድም በመመልከት ላይ እያሉ ነው ።

ይህም ወር ታኅሣሥ መጨረሻ አካባቢ ስለሆነ አግሌቃውያን ወጣቶች ወደ ክርስቲያኖች ጠጋ ብለው እናንተ ክርስቲያኖች ልደተ ጥምቀት እያላችሁ የምትጨፍሩበት ጊዜ ደረሰላችሁ ይላሉ ፈገግ እያሉ በጨዋታ መልክ በዚህ ጊዜ ክርስቲያን ወጣቶችም መግር ደግነውና በትዕግሥትና በዕርጋታ እውነተኛውንና ትክክለኛውን መልስ ሲሰጡ እግዚአብሔር ሰውን በአርአያውና በአምሳሉ የፈጠረው ሰው ክብሩን እንዲወርስ ስሙን እንዲቀድስ ነው በዚህም ቅዱስ ዓላማ መሠረት ስሙን መቀደሳችንና ማመስገናችን እንጂ መጨፈራችን አለመሆኑን እንድታውቁልን እንፈልጋለን የሚገባም ነው በማለት ይመልሱላቸዋል ።

ከዚህ በኋላ ግን ቀደም ብለው ለመነጋገር ሲጀምሩ የነበራቸውን ጠባይ ለወጥ አድርገው እንደ ሰከረ ሰውቀለል ቀለል እያደረጋቸው በአገራቸው ቋንቋ ሣይሆን በአረብ ቋንቋ የእግዚአብሔርን ስም ወላሂ ብለው እየጠሩ ሳቅ ሳቅ ማለቱን መዘባበት፤ ማሽሟጠጡን ቀጠሉና አላህ አንድ ነው አይወልድም አይወለድም ለመሆኑ እናንተ ወረደ ተወለደ ስትሉ አታፍሩም? በውሃ መጠመቅ ቢሆን ልጅነት ያሰጣል ስትሉ ምን ማለታችሁ ነው ? በማለት ጥያቄያቸውን ሰፋ አድርገው በስብከት መልክ ያቀርቡታል ።

በዓላማቸው ቀደም ብሎ በቢላል መጽሔት ከተሰጠው የውኸንብር ቃል ጋር ይህ ቅስቀሳ ተደምሮ አሳማኝ ትምህርት ይሆንና ተቀባይና ተከታይ ለማግኘት ነበር ሙከራቸው ።

ነገር ግን የሰውና የእግዚአብሔር ፈቃድ የተለያየ ስለሆነ በአሰቡባት ሳይሆን ባላሰቡበት መንገድ ሥራውን ሠራ ይኸውም መንፈሳውያን ወጣቶች በተማሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ተጠቅመው ወርጂ ተወልጂአድናችኋለሁ ብሎ እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን ከሰጣቸው ተስፋ ጀምረው አግሌቃውያን ኦሪትን ነቢያትን እናውቃለን ስለሚሉ ስለ ኦሪት ፤ ስለ ነቢያት እየገለጹ ነቢያት እነ ኢሳይያስ ፤ እነ ሕዝቅኤልና እነ ዳንኤል የተናገሩትን በመጥቀስና በመተርጎም አንድ በአንድ ቁልጭ አድርገው ያስረዱቸዋል ።

እንደዚህ ባለው ውይይት ላይም መንፈስ እግዚአብሔር ስለማይለይ በእግዚአብሔር መንፈስ ትምህርቱ ስለተገለጸላቸው እነዚህ አግሌቃውያን የአመለካከታቸውን አቅጣጫ ዘወር አድርገው ረጋ ባለ ስሜት እያዳመጡ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን መወለድ ፤ መጠመቅ ፤ መሞት ፤ መነሣት የሚያስተባብሉት እውነተኛ ስላልሆነ ያለምንም ማመንታት ተቀበሉት ። አሁን ወጣቶች እንዲህ ዓይነቱን የሃይማኖት ውይይት ለማካሄድ የጀመሩት ከትምህርት ክፍላቸው ለዕረፍት በወጡበት ጊዜ በ፲፭ ደቂቃ ብቻ የሚያልቅ መስሏቸው ስለነበረ ነው ። ከውይይቱ ውስጥ ከገቡ በኋላ ግን በተለይም የተዋሕዶ ሃይማኖትን ምሥጢር ማመሥጠርና መተንተን ከጀመሩ በኋላ ራሳቸው ተንታኞችም ሆኑ አድማጮች ከአሉበት ቦታ በተመስጦ ተነጥቀው በተዋሕዶ ምሥጢር ሲዋኙ የዕረፍት ጊዜያቸውና በጠቅላላው የዕለቱ የትምህርት ጊዜ አልፎ ተማሪዎቹ ሁሉ ወደ የቤታቸው ሲሄዱ እነርሱ ቀርተው ከ፲፪ሰዓት በኋላ በገድ ፣ በአሣርና በናፍቆት በዕንባ እየተራጩ ነው የተለያዩት ምክንያቱም የምሥጢሩ ጥልቀት የሃ

ተከታዩን በ፳፫ኛው ገጽ ይመልከቱ



# የመቄት አስደናቂ ተአምር

በወሎ መቄት በአምሳለ ክርስቶስ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን አካባቢ አስደናቂ ተአምር የተከሠተ ስለመሆኑ በቁጥር ፪ ልግን ተዋሕዶ መጽሔት ባጭሩ ገልጸልናል ።

እንደሚታወቀው በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን አስደናቂ ተአምር ያልታየበትና ያል ተሰማበት ጊዜ የለም ። በየጊዜውም እየተፈጸመ ነው ።

በብዙ የሀገራችን ክፍሎች በተለያዩ ገዳማትና አድባራት በራእይ እየተገለጹ ተቆፍረው የወጡ ንዋያተ ቅድሳትና የታሪክ ቅርሶች እጅግ በጣም ብዙዎች ናቸው ይህም በየጊዜው እየተገለጸ ነው ።



መልአከ ሣህል ሣህሉ ማተቤ የደብሩ አስተዳዳሪ

ከነዚህም መካከል ከምድር ውስጥ ተፈልፍሎ የወጣውና አሁን በአገልግሎት ላይ የሚገኘው ደብረ ጽባሕ መድኃኔ ዓለም የተባለው ቤተ መቅደስ ሲሆን በጥንተ ስሙ ጠንበቆት ኪሮስ ይባላል ። ይሁን እንጂ የዚች ኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪካዊ ዝና ከጽንፍ እስከ ጽንፍ እየተነገረ የማያውቋት እንዲያውቋት የሚያቁአትም የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ እያደነቁ እንዲያወሩ ያስቻላቸዋል ።

ትላንትና በአያቶቻችን ዛሬ በጠንካሮች ልጆቻቸው ነገም እግዚአብሔር በሚመርጣቸውና ለታሪክ በሚታደሉ ተተኪ የልጅ ልጆቻቸው ቅርሶች ከከርሠ ምድር እየወጡ ሕያው ታሪካችንን ለማየትና ለማሳየት በቅተናል ። ይልቁንም የእግዚአብሔር መንፈስ ያልተለያቸው ተአምራዊ ኃይልን የሚሠሩ ጠበሎች ከሸክላ አፈር በተሠሩ ኩስኩስቶች (ማሰሮዎች) ውስጥ የተገኙ ውሃዎች በእግዚአብሔር ኃይል ሕሙማንን በተለይም ዓይናቸውን የተከለሉ ወገኖቻችንን ሲያድኑ ማየት ለኦርቶዶክስ ተ/ ቤ/ ክ/ ምዕመናን የተለየ ክብርን የሚያጎናጽፍ ይሆናል ። ከዚህም ጋር በውስጧ ለሚገኙት ተከታዮችዋ ታላቅ የምሥራች ነው ።

እንግዲህ ስለዚህ አስደናቂ ተአምር ዓይናን አብራው መድኃኔ ዓለም ስለተባለበትና ንዋያተ ቅድሳቱ ስለተገኙበት ሁኔታ እንዲያብራሩልን የአምሳለ ክርስቶስ መድኃኔዓለምን ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ መልአከ ሣህል ሣህሉ ማተቤን አነጋገርናል ። መልሱንም እንደሚከተለው አቅርበናል።

ጥያቄ ፣ በሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት በመቄት ወረዳ ልዩ ስሙ ቀበሌ ፴፭ በተባለውና አምሳለ ክርስቶስ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ተአምራታዊ ኃይል ያላቸው ንዋያተ ቅድሳት እንደተገኙ ተነግሮአል እንዴት እንደተገኙ ዝርዝር ታሪኩን ለአንባብያን ቢያብራሩልን ? ።

መልስ የተገኙት እነዚህ ታሪካዊ ኩስኩስቶች (ማሠሮዎች) ዘጠኝ ናቸው ዘጠኙም ንጹሕ ውሃ እንደተሞላባቸው ነው የተገኙት ፣ የተገኙትም ርዝመቱ ፫፱ ሜቴር ከፍታ ካለው ቋጥኝ ውስጥ ተቆፍሮ ሲሆን እነዚህና ሌላም ንዋየተ ቅድሳት በምድር ውስጥ እንዳሉ በሕልም አየሁ እያሉ መናገር የጀመሩተ መሪጌታ የሻው እጅጉ ናቸው ። በአሁኑ ሰዓት በዚሁ ታሪካዊ ሕልማቸው መነሻ መልአከ ምሥጢር ተብለዋል ። ይሁንና በዚሁ ሕልም ምክንያት ቁፋሮ ተጀምሮ ዘጠኙም ኩስኩስቶች ውሃ እንደተሞሉ ሊወጡ ችለዋል ። ዓይን አብራው መድኃኔ ዓለም የተባለውም በኩስኩስቶች ውስጥ ያለው ውሃ ብዙ እውራንን ዓይናቸውን በማብራቱ ነው ዓይን አብራው ብለው የተናገሩትም ዓይናቸው ከበ

ወደ ገጽ ፲፰ ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

ራላቸው ዕውራን እንደኛው መሪጌታ ናቸው ።

ልሣነ ተዋሕዶ እነዚህ ንዋያተ ቅዱሳት ሲወጡና ዕውራን ዓይናቸው ሲበራ በቦታው ላይ የተገኙ ሰዎች ነበሩን ?

መልስ የመጀመሪያው ኩስኩስት የወጣው ሕልሙን ባዩትና በሰበካው ካህናትና ምዕመናን ቁፋሮ ነው ። ዕለቱም ጥቅምት ፴ ቀን በመጥምቁ ቅ/ዮሐንስ ወርሐዊ በዓል ዕለት በመሆኑ አንድ ታሪክ እንዳለው እኔን የሚሰማኝ ነገር አለ ። በሁለተኛው ጊዜም ኅዳር ፴ ቀን በዓለ መጥምቀ መለኮት ቅ/ዮሐንስ ሲሆን በዚሁ ዕለት ሀ/ የሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ፣ ለ/ የሰሜን ወሎ መስተዳድር ኃላፊ አቶ ውዱ ካሣው ሐ/ የመስተዳድሩ ባሕልና እስፓርት ሚኒስቴር ባልደረቦች መ/ የመቄት ወረዳ ቤተ ክህነት ኃላፊዎች ፣ ሠ/ በጠቅላላ የ፫ ገበሬዎች ቀበሌ ማኅበራት ሕዝብ ተገኝቶአል ።

ልሣነ ተዋሕዶ ጠበሎች እንደ ተአምር የሚነገርላቸው ዓይን አብራዎች መሆናቸውንና ልዩ ልዩ ሕሙማንን የሚፈውሱ መሆኑን ተረድተናል እነማንን እንዳዳኑ ሊያብራሩልን ይችላሉ ?

መልስ አዎ ጥቂቶችን ለማብራራት እሞክራለሁ ፣ ፩/ ለ፲፭ ዓመታት ዓይናቸውን ተከልለው የኖሩ የዕድሜ ባለፀጋ የሆኑት መዘምር ደሴ ደመቀ የናቁውን ሲቀቡ ዓይናቸው በርቶአል ። ይህም ተአምር የተፈጸመው ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ በተገኙበት ዕለት በመሆኑ ብፁዕነታቸው የዓይን ምስክር ናቸው ።

፪/ በዚሁ መቄት ወረዳ ውስጥ ነዋሪ የሆኑት አቶ አሜዋች ይብታው ዓይናቸው በርቶአል ።

፫/ የአብዲ ቆም ቅ/ጊዮርጊስ አገልጋይ የሆኑት መምህር መርዓዊ ተበጀ ዓይናቸው ለማየት በቅቷል ።

፬ኛ/ ስማቸውን ያልመዘገብኩትና ዓይን አብራው መድኃኔ ዓለም ብለው የተናገሩ አንድ መምህር ወደ ቤታቸው ከገቡ በኋላ ዓይናቸው በርቶ የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል ።

፭/ በቁርቁር ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የሆኑት መሪጌታ ካሣ ተሰማ መላ ሰውነታቸው አብጦና ዓይናቸው ተከልሎ ሲኖር በዚሁ ጠበል ካለባቸው ደዌ ተላቀዋል ዓይናቸውም በርቶአል ።

፮/ ወ/ሮ የሺሐረግ ሰጠኝ ከሆዳቸው ውስጥ የሥራይ በሽታ የወጣላቸው ሲሆን በላያቸው ላይ አድሮባቸው የነበረው ርኩስ መንፈስ ጮሆ ለቆአቸዋል ።

፯/ ከአሰብ የመጡ አቶ ወንድም አገኘሁ የተባሉ በአባለ ዘራቸው አካባቢ ሽንት በመከልከል ሲኖሩ በዚሁ ጠበል ለመዳን ትለዋል ።

፰/ ከእነዚህ ሌላ ቁስል ነክ ጉርምጥ ችፌ ነቀርሳ የመሳሰሉ ያለባቸው ሁሉ በዚሁ ጠበል ድነዋል ።



ልሣነ ተዋሕዶ/ በዚሁ አምሳለ ክርስቶስ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ሌሎች ጠበሎች ነበሩ ? እነሱስ በማን ስም የተሰየሙ ነበሩ ?

መልስ በቦታው ላይ በጣም የታወቁና የነበሩ ፫ ጠበሎች አሉ ከእነዚህም አንዱ በመድኃኔ ዓለም ስም የተሰየመ ሲሆን ሁለቱ ግን የማን እንደሆኑ አልታወቁም ። በአዳኝነታቸው ግን የታወቁ ናቸው ። አሁን ግን በእኔ አእምሮ ውስጥ የሚመላለሰው አንደኛው የመጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ ነው ብየ እገምታለሁ በወርኃዊ በዓሉ የሚፈጸሙ ፈውሶች ስለሚታዩ ነው ።

ልሳነ ተዋሕዶ በመጨረሻ የሚያስተላልፉት መልእክት ካለ ? የወጡት ንዋያተ ቅድሳት ታሪካዊነት ስላላቸው ሁሉም ሰው ቢመለከታቸው ሁልጊዜውም ይቀዳል ግን ኩስኩስቱ አይጎድልም ይህ ሌላው ተአምር መሆኑን በቦታው ላይ ተገኝቶ በዓይን ማየት ለበለጠ ምስክርነት ያበቃል ዳኑ የተባሉትን ሕሙማን በዓይን ዓይቶ በእጅ ዳስሶ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥም ለጋዜጠኞች መልካም ይሆናል እላለሁ ።

፱/ በከርሠ ምድር ውስጥ ገና የሚኖሩ ንዋያተ ቅድሳት እንዳሉ መጋቤ ምሥጢር የሻው ስለሚናገሩና በአሁኑ ሰዓት በዚያው ቦታ ላይ በጸሎት ተወስነው ስለሚገኙና ቦታውም በአጥር ተከልሎ ስለሚጠበቅ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን ቦታ ለማየት እግዚአብሔር እንዲፈቅድልህ እንጸልያለን በማለት መልሴን አጠቃልላለሁ ብለዋል ።

እኛም ይህን አስደናቂ ተአምር በዚህ ብቻ ሳናበቃ የሀገረ ስብከቱን ሊቀ ጳጳስና ዓይናቸው በራ የተባሉትን ግለሰቦች በአካል አነጋግሮ ከንዋያተ ቅድሳት ጋር በመጽሔት ለምእመናን ማቅረብ ጠቃሚነት እንዳለው በማመን ወደ ቦታው ለመጓዝ ምኞት አለን ።

ሊቀ ካህናት በለጠ አበበ

ከ፲፱ኛው ገጽ የዞረ

## የሰበካ ጉባኤ ...

ቃለ አዋዲውምከጊዜ ወደ ጊዜ ለወቅቱ እንዲስማማ እየሆነ እየተሻሻለ መጥቷል ።

ክፍል ፩

### የተሻሻለው ቃለ ዓዋዲ ፣

፩/ ቤተ ክርስቲያን በምእመናን አንድነት መደራጀቷ ፣ በሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አስተዳደርም መመራቷ ከጥንት ጀምሮ ያለ እንጂ አዲስ አለመሆኑና አመራሯና አስተዳደርዋም በአበው ተያይዞ የመጣ መሆኑ የታመነ ነው ። የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር

ተከታዩን በ፳፩ኛው ገጽ ይመልከቱ

## እናቶች ለልጆቻቸው

መንፈሳውያን እናቶች ልጆቻቸውን በእምነት ፤ በሥነ ምግባር ፤ በጥበብ ፤ በሞገስ ኮትኩተው ያሳድጓቸዋል ። የእናቶችና የልጆች መስማማት ለቤተሰብ ሰላም ፤ ለአንድ ሀገር መንፈሳዊ ፤ ማኅበራዊና ሁለንተናዊ እድገት ወሳኝ ከሆኑት መሠረታዊ ነጥቦች አንዱና ዋነኛው ነውና የልጆች አስተዳደግ ከመንፈሳዊ አገልግሎትና ከማኅበራዊ እንቅስቃሴ ጋር በአግባቡ ቢካሄድ እናቶችና የወንጌል መምህራን ለቤተ ክርስቲያን እድገት የሚያደርጉት ጥረት የሰመረ ውጤቱም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ያማረ ይሆናል ።

የእምቢባይነት ጠባይ ያሸነፋቸው የልጆቻቸውን ባሕርይ ለመግታትና እድገታቸውንም ከመንፈሳዊ አገልግሎት ጋር ለማዛመድ በጥረት ላይ የሚገኙ እናቶች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም ። ጥረታቸውንም በዚህ ሁኔታ ያካሂዱና ለውጤት የበቁ እናቶች የመናራቸውን ያህል ይህንን ተግባር መፈጸም ተስናአቸው ሕይወታቸውን በሐዘን የሚያሳልፉ ብዙዎች ናቸው ።

እነዚህ እናቶች የልጆቻቸውን አስተዳደግ በእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል አለማድረጋቸውና ከመንፈሳዊ እድገት ጋር ማስተዋወቅ አለመቻላ

ተከታዩን በ፳፪ኛው ገጽ ይመልከቱ

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዓለም አቀፍ

ከ፲፫ ገጽ የዞረ

ራቸውን ግንኙነት ለማደስ በቅርቡ የጋራ ውይይት ሲያካሂዱ ቆይተዋል ።

ለዚህም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ባላቸው የዓለም አቀፋዊ አመለካከት በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት የነበሩ ልዩነቶች ተወግደው የአንድነት መንፈስ እንዲፈጠር ሆኖ አል ። ይህም ይታወቅ ዘንድ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ጥሪ መሠረት በብፁዕ አቡነ ቢሾይ የእስክንድርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ የሚመራ ከፍተኛ የልኡካን ቡድን ያካተተ በወርኀ የካቲት ፲፱፻፹፯ ዓ/ም በአዲስ አበባ በመንበረ ፓትርያርክ አዳራሽ ከ፫ ቀናት ያላነሰ ስብሰባ ተደርጎ ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት የጋራ ስምምነት ላይ ደርሰዋል ከላይ ለትምህርተ ጥቅስ ያህል የተጠቀሰው ቃል ከዚህ ላይ ለምሳሌነት ቢጠቀስ ተገቢ ሆኖ ስለተገኘ መጥቀስ የሚከፋ አይመስልም ።

እግዚአብሔር አምላክ በዓለም አቀፋዊ ይዘት የቤተ ክርስቲያንን በሮች ለመክፈት ሲፈልገው የቤተ ክርስቲያንን ድምጽ ለሌላው ዓለም ሊያሰማው ሲሻ ተግባራትን የሚፈጽምና የሚያስፈጽም መንፈሳዊ አባት ያስነሳል ። እንዲሁም ለዘመናት የተለያዩትን አብያተ ክርስቲያናትን እንዲቀራረቡና በዓለም አቀፋዊ ሁኔታ ላይ የተመረኰዘ መተሳሰብ በመካከላቸው እንዲሰፍን የሚጣጣር አባት ያስገኛል ። በእውነት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንና የእስክንድርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በስምምነት ፤ በአንድነት ፤ በመተባበር ፤ በፍቅርና በሰላም በዓለም አቀፋዊ መንገድ እንዲሄድ የመራሒነቱን ፈለግ ስለአሳዩአቸው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስን ታሪክ ዘወትር ሲያወሳቸው ይኖራል ቢባል ማጋነን ሳይሆን ትክክለኛውን ገጽታ (ኢሜጅ) ለማስቀመጥ የተሰነዘረ ሐሳብ መሆኑን ለማሳሰብ እንወዳለን ።

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ዓለም አቀፋዊ አመለካከት ስልት መሠረት በሊቃነ ጳጳሳት ደረጃ የሚመራ ቡድን በተለያዩ ዓመታት ወደ ካይሮ በመሄድ ልዩነትን ለማስወገድ ከኮፕቲክ ጳጳሳት ጋር በካይሮ ላይ በዛ ያሉ ስብሰባዎች ማድረጋቸው የሚዘነጋ አይደለም ። አሁን የተገኘው የጋራ ስምምነት በእነዚህ ስብሰባዎች በተደረገው ውይይት ውጤት መሆኑን ለመግለጽ ነው ። በወርኀ የካቲት ፲፱፻፹፯ ዓ/ም በአዲስ አበባ በመንበረ ፓትርያርክ አዳራሽ ውስጥ የተካሄደው ስብሰባ ግቡን ሊመታ የቻለው ከካይሮ ጀምሮ ሲካኼዱ በሰነበቱ ውይይቶች ነው ለማለት ይቻላል ። ከሁሉ በላይ ግን የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ መንፈሳዊ አመራር በዚህ በኩል ያደረገው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ስለሆነ ታሪክን ለባለ ታሪክ እንተዋለን ።

በወርኀ የካቲት ፲፱፻፹፯ ዓ/ም በተደረገው ስብሰባ ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ወክለው የተገኙት ፤

፩/ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የትግራይ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ፣

፪/ ብፁዕ አቡነ ገሪማ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ፤

፫/ ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ዋና ጸሐፊ

፬/ ብፁዕ አቡነ ገብርኤል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የውጭ ግንኙነት የበላይ ኃላፊ ናቸው ።

ስብሰባውንም በጸሎት ቡራኬ የከፈቱት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ናቸው ።

ተከታዩን በ፳፩ኛው ገጽ ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

# የሊቃውንት ዓምድ

## የሊቁ የክ/ ዮሐንስ ታሪክ ሁለተኛ ክፍል

ሊቁ ክፍሌ ዮሐንስ ከጎንደር አድባራት ለይቶ መርጦ ኑሮውን በደብረ ብርሃን ሥላሴ ያደረገው ስለምንድነው ብሉ መጀመሪያ ጎንደር የገባለት የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ያደረው በደብረ ብርሃን ሥላሴ ስለነበር ነው በበነጋውም ወይም በማግስቱ መልካም አጋጣሚ ሆነለትና አምደ ሃይማኖት እጨጌ በትረ ጊዮርጊስ ብዙ ሊቃውንት አስከትለው በዚያ ቦታ ተገኙ እሱም በኢቃቤ ሰዓት ቀርቦ እጅ ነስቶ በፊታቸውም ቆመ እጨጌ በትረ ጊዮርጊስም የተማረ ሊቅ ሰው ስለሚወዱ ከዚያ አስቀድሞ የሚያውቀውንና ያጠናውን ትምህርት ጠየቁት ክ/ዮሐንስም ቅኔና መጻሕፍተ ሐዲሳትን ጠንቅቆ ያወቀ መሆኑን መልሶ ነገራቸው እጨጌውም በትምህርቱና በአነጋገሩ ተደንቀው የቀረውን የመጻሕፍተ ብሉያት ጉባኤ ከሐዋርያ ክርስቶስ ድርሰትን ከአባ ስብሐት ለአብ እንዲማር አዘውት እርሳቸውም እስከ መጨረሻ የሚረዱት መሆኑን ተስፋ ሰተውት ወደ አጼ ፋሲል ቤተ መንግሥት ተመለሱ እርሱም እጅ ነሥቶ ተመልሶ እንደ ተነገረው መጻሕፍተ ብሉያትን ከሐዋርያ ክርስቶስ መንፈሳዊ ድርሰትን ከአባ ስብሐት ለአብ አጠና መቼም ለርሱ ቀለምአስቸጋሪሆና የተጨነቀበት ጊዜ ስለሌለ ሁሉንም አጠናቆ በደብረ ብርሃን ወንበር ዘርግቶ ጉባኤ አስፋፍቶ ያስተምር ጀመር የመጀመሪያ ምርጫው ይሄ ነው በተጨማሪ ጎንደር ደብረ ብርሃን ለኑሮ የመረጠበት ስለ አራት መንፈሳዊ ነገር ነው ።

፩- ቦታው ከከተማ ውጭ በመሆኑ ስለ ጸጥታው
፪- እርሱ መናኝ ባሕታዊ ነውና ለማስተማርና ለጸሎት እንዲመቸው ።
፫ ሥጋዊም ሆነ መንፈሳዊ ክብር ያገኘበት ቦታው ስለሆነ ፤
፬- መዋዕለ እድሜውን ፈጽሞ በአረፈ ጊዜ መካነ መቃብሩ የሚወሰነው በዚያ እንደ ሆነ በመንፈስ ቅዱስ ስላወቀው ነው ።
ይሁን እንጂ ወደ መካከለኛው ከተማ ገብቶ የሚታይበት ጊዜ አለ ።

፩ኛ/ ስለ ክብረ በዐል ነው ታኅሣሥ ፳፬ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ክብረ ልደታቸው ነሐሴ ፳፬ ዕለተ እረፍታቸው ግንቦት ፲፪ ፍልሰተ አጽማቸው ስለሆነ የዚህ መታሰቢያ በዓል በአደባባይ ተክለ ሃይማኖት በመንፈሳዊ ልዕልና ስለሚከበር በደብሩ ተገኝቶ ቅኔውን ሲያወርደው ውሎ ድሕረ ቁርባን ሲሆን ከሚረዱት ከቂስ እጼ

ተከታዩን በ ፳፬ኛው ገጽ ይመልከቱ

## የመጽሐፍ ቅዱስ ቀን በዓል

ከ ፲፩ኛው ገጽ የዞረ

ቅርያችና ዓይነቶች እያሳተመና ለዓይነ ሥውራን በብሬል ፤ ማንበብ ለማይችሉ በካሴት እየቀረጹ፣ በማሠራጨት በብዙ ሚሊዎን የሚቆጠሩ ወገኖች የእግዚአብሔር ቃል እንዲደርሳቸው ያልተቆጠበ ጥረት አድርጓል ። በዓላት ጠቀስ የሆኑ መልእክቶችን ምርጥ የመ/ቅዱስ ቃላትን የያዙ በራሪ ጽሑፎችን በየጊዜው እያዘጋጁ ለአብያተ ክርስቲያናት ማቅረብም ከዝርዝር ተግባራት አንዱ ዘርፍ እንደሆነ የማኅበሩ ጠጸሐፊ አቶ ከበደ ማሞ ገልጸዋል ።



አቶ ከበደ ማሞ የማኅበሩ ጠ/ጸሐፊ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ በዓሉን በጸሎት ቡራኬ ሲዘጉ ባስተላለፉት መልእክት በክርስቶስ ስም ያሉ የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ተከታዮች ሁሉ ኃላፊነታቸውን በምክርና በውይይት መወጣት እንደሚኖርባቸው ጠቅሰው የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ይህን ዓላማ በሥራ ለመግለጽ ፣ሚያሳካ የመጀመሪያ እንቅስቃሴ ማድረጉ የሚመስገን መሆኑን ገልጸዋል ። ቅዱስነታቸው "የእግዚአብሔር ሥልጣን የማይገዛው ቀንና ሌሊት ባይኖርም እንደዚህ ያሉት ዕለታት እግዚአብሔርን በማኅበር እንድናመሰግንባቸውና ስለሰው ዘር ሰላምና ደኅን

ተከታዩን በ፳፩ ኛው ገጽ ይመልከቱ





ከ፩ኛው ገጽ የዞረ


ነት እንድንወያይባቸው የተለዩ ናቸው ብለዋል ።

ፓትርያርኩ መልእክታቸውን በመቀጠል የእግዚአብሔር ቃል ስነ ፍጥረት ሁሉ የተገኘበት ስለሆነ ሕይወት ነው ። ኢትዮጵያ ከሙሴ ኦሪት ጀምሮ የሃይማኖት መጻሕፍትን የተየተቀበለች ስለሆነ መ/ቅዱስ ለኢትዮጵያ አዲስ አይደለም ኢትዮጵያ ከእግዚአብሔር ጋር ያላት ግንኙነት በመጽሐፍ ቅዱስ ገላጭነት የተመሠከረ ስለሆነ ሰውሠራሽ አይደለም

ኢትዮጵያውያን ጌታ በቤተ ልሔም ሲወለድ በቦታው ተገኝተዋል ። ለአምላክነቱና ለጌትነቱ የሚገባውን መባዓ አቅርበዋል ። ሀገራችን ጥምቀትንም በፈቃድዋ የተቀበለች ትንቢት የተነገረላት ተስፋውንም በተግባር የገለጸች ሀገርናት ።

ኢትዮጵያ ሃይማኖትን በቀዳሚነት መቀበል ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ጋር አብሮ ለመኖር ባላት ፈቃድና ፍላጎት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት መሥራችና ቋሚ አባል ናት አብሮ የመሥራት ፍላጎት የሌላትና እንደኋላ ቀር አድርገው በመመልከት የተሳሳተ አሳብ የሚሠነዝሩ ካሉ አስተያየታቸውን ፣ ሊያስተካክሉ ይገባል ። በርግጥ አሁንም በእምነቷና ሥርዓቷ የራሷ የሆነውን በጥንቃቄ ጠብቃ ስለምትገዝ ሌላ አዲስ ኅብረት ፈጠረች ተብሎ እንዳይተረጐም ያስፈልጋል ።

ከመጽሐፍ ቅዱስ የማንማረው ምንም ነገር የለም ለሕይወት መመሪያ አስፈላጊ ለሆኑ ትምህርቶችና መመሪያዎች ሁሉ ምንጩ መጽሐፍ ቅዱስ ነው እርቅን ሰላምን ፤ ፍቅርን በሌላው እንዳንፈርድ መጠንቀቅን ፤ ፡ጻዳትንና አብሮ የመኖርን ጥበብ ሁሉ ያስተምረናል ። መ/ቅዱስን በስሙ ብቻ ተቀብሎ በውስጡ ያለውን ትምህርት በሥራ ለመተርጐም ያስጠይቃል ። በጊዜያዊ ሕይወታችን የእግዚአብሔር ቃል እንዲኖርበት ያስፈልጋል ። እግዚአብሔር በውስጡ የሌለበት ሕይወት በጨለማ ይኖራል ።



የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎችበበዓሉ ላይ እንደተገኙ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለመ/ቅዱስ ማኅበር ዋና መሥራች እንደመሆኗ የማኅበሩ ዕድገትና የሥራ እንቅስቃሴ ሁሉ ያስደስታታል ። እምነቷንና ሥርዓቷን ጠብቃ ከሌሎች ወንድሞችና እህቶች ተባብራ ለመሥራት ምን ጊዜም ፈቃደኛ ነች። ግን ኅብረት አንድ ቀን በአንድ ቦታ መሰብሰቡ ብቻ ሳይሆን ዓላማውን በሥራ መተ

ተከታዩን በ፳፪ኛው ገጽ ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

# እናስተዋውቃችሁ

በዛሬው እናስተዋውቃችሁ ይዘንላችሁ የቀረ ብነው የኢትዮጵያውያን ኩራት የሆነውን ለአንድ ቀን ብቻ ፀበል የሚፈልቀውን አስደናቂታሪክ ነው ።

ይህችም የታሪክ ቦታ በደቡብ ወሎ ውስጥ በአግራ ሳይንት ወረዳ የምትገኘውን የቸር ተክል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ናት ።

በዚች ቤተ ክርስቲያን ጥንታውያን የሆኑ ቅር ሶች ይገኛሉ ። ከቅርሶቹም አንዱ ታላቁ ሐዋርያና ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ዘደብረ ሊባኖስ የእጅ መስቀል ዕድሜው ፯፻ መቶ አመት የሆነው ከአባ ኢየሱስ ሞዓ የተሰጣቸው የእጅ መስቀል ይገኛል ።

ቸር ተክል የተባለችውም አቡነ ተክለ ሃይማ ኖት ፲፩ ዓመት ሱባኤ ገብተው ስለፀለዩባት አቡነ ተክለ ሃይማኖት የተከሉት ወርካ ለምልሞ ስለተገኘ ቸርተክል (ደግ ተክል) ተባለች በዚህም ምክንያት ቸር ተክል ማርያም ትባላለች ቦታዋ የምትገኘው ከበሾሎ ወንዝ አጠገብ ሲሆን ከበረሃው ውስጥ በመ ሆኗ በዓመት አንድ ቀን የኅዳር ማርያም ብቻ ትከ ብራለች ከተራራ ጥግ ላይ ነው ያለችው አንድ ትልቅ ወርካ እድሜው ከ፩፻ ዓመተ በላይ የሆነው ከእድሞው አጠገብ ከማርገጃው ላይ ይገኛል ።

ወርካው በጣም ትልቅና ግዙፍ ሲሆን ከመስ ከረም ጀምሮ እስከ ግንቦትና ሰኔ ድረስ ከፀሐዩ ለመ ዳን ብዙ እንስሳትና አእዋፍ ይጠለሉበታል ብዙ ሰዎችም ያርፉበታል ። መጋቢት ፳፩ ቀን ለአንድ ቀን ብቻ ከወርካው ሥር አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከተከሉት ስር ፀበል ይፈልቃል ፀበሉም ሲፈልቅ ወደ ሰማይ እየዘለለ ሲወጣ ከየክፍለ ሀገሩ የተሰበሰ ቡት በሽተኞች እንደ ቤተ ሳይዳ እኔ ልጠመቅ እኔ ልጠመቅ በማለት ይሽቀዳደማሉ ። መጋቢት ፳፩ ቀን ጧት ፀሐይ ከመውጣቱ አስቀድሞ ወፍ ሲንጫጫ የፈለቀው ፀበል ማታ ጀንበር ስትጠልቅ ያቆማል ።

ይህ በጣም ያስደንቃል በአራቱም ማዕዘን ከሩቅም ከቅርብም የሚመጡት በሽተኞች ተድመው ሲጠመቁ ይድናሉ ይህንንም ታሪክ የሚያውቁ ታላላቅ ሊቃውንት ለምሳሌም አለቃ ኤልያስ ነቢየ ልዑልን እነ መላከ ፀሐይ ቀለመወርቅንና መምህር ከሃሊ በቃሉን ጠይቆ መረዳት ይቻላል ። እንግ ዲህ ይህች ቤተ ሳይዳ የሆነችውን ፀበል በበጋ ቀርቶ በክረምት እንኳን አካባቢው ውኃ የማይገኝበትመ ሬት መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን በወርኃ መጋቢት ፳፩ ቀን በእለተ እሑድ አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማ ኖት ከሐይቅ ሲመለሱ ወደዚሁ ቦታ በመሄዳቸውና ከላይ በጠቀስነው ዕለት መቋሚያቸውን ቢተ ክሉት እንደበቀለና ዋርካውንም ተክለውት እንደ ሄዱ ታሪኩ ያስረዳል ። ስለዚህ በዛሬው እናስተ ዋውቃችሁ እዚህ ላይ እናልብና በሚቀጥለው እናስ ተዋውቃችሁ አስደናቂውንና አስገራሚውን ሰው ይዘንላችሁ እንቀርባለን ።

ሊቀ ብርሃናት መርቆሬዎስ አረጋ

# የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች ምስክርነት

ከ፲፯ኛው ገጽ የዞረ

ይማኖቱ ፅንዓት ለሰው ልጅ ከእግዚአብሔር የተ ሰጠው ተስፋ ምን ያህል እንደሆነ ስለተረዱና ስለ ረኩ አሁንም እንደገና ሲወያዩ ውለው ሲወያዩ ቢያድሩ የሚሰለቹ አይመስሉም ነበር ።

ቢሆንም ከክርስቲያኖች ወጣቶች በተሰጣቸው ማብራሪያ የሚበቃቸውን ያህል ግንዛቤ ስላገኙ ከዚች ሰዓትና ደቂቃ በኋላ የክርስትናን ሃይማኖት ከራሳቸው ሃይማኖት ጋር ማመዛዘንና ማወዳደር ጀመሩ ። እነዚህ አማሌቃውያን ወጣቶች ቀንም ሌሊትም ይህን የክርስተናን እምነት ጉዳይ በሕሊና ቸው ሲያወጡ ሲያወርዱ ሲአሰላስሉት ሕሊናቸውን ዳኛ አድርገው ፍርድ ስጥ ሲሉት አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሕሊናቸውን ሚዛን አድርገው ራሱን ሃይማ ኖቱን ሲመዝኑት አሁንም በዓይነ ሕሊናቸው የሃይ ማኖቱን ምሥጢር አተኩረው ሲመለከቱት ውጤቱ አንድ ይሆናል ። በዓይነ ልቡና ሲታይም «መኑ ዘደመሮ ለብርሃን ምስለ ጽልመት» የሚለውን ቃል ሕሊናቸው ይተረጉመዋል ።

ይተነትነዋል ። በዳኝነት በኩልም ቢሆን ሲመረም ሩትና ሲያጣሩት እውነት የት እንደ አለ አረጋግ ጠዋል ። በዚህ ጊዜ ነው ጉድ ሊፈላ የቻለው ለምን ቢባል እነዚህ ወጣቶች ወደ በላያቸው አማሌቃው ያን ሃይማኖት መሪዎች በመሄድ የእስልምናሃይማኖት

ተከታዩን በ፳፮ኛው ገጽ ይመልከቱ

## የመጽሐፍ ቅዱስ ቀን በዓል

ከ፳፩ኛው ገጽ የዞረ

ርጎሙ ነው እነሱና እኛ የሚለውን ተሸጋጋሪ ሃሳብ ትቶ ሕዝቡን በኅብረት ማገልገል ለአንድ ዓላማ መሥራት ያስፈልጋል ። በማለት ሰፋ ያለ መልእ ክት አስተላልፈው በዓሉን በጸሎተ ቡራኬ አስናብተዋል ። የመ/ቅ/ማኅበርም ምእመናንበአ ባልነት በመመዝገብም ሆነ በበጎ ፈቃድ ማኅበሩን በገንዘብና በማቴሪያል እንዲረዱ ጥሪውን አቅር ቦአል ።



# ቅዱስ ፓትርያርኩ . . . .

ከ፩ኛው ገጽ የዞረ

ካህናቱ በመንፈሳዊ አገልግሎት በኩል ሥራ ላይ ሲውሉ ለየት ባለ ሁኔታ እንዲታዩ ለመ ዘምራኑና ለቀሳውስቱ ካባ ለዲያቆናቱ ተስ ማሚ የሆነ የደንብ ልብስ አሰፍቶ ሰጥቷ ቸዋል ። በጸሎተ ፍትሐት በማኅሌትና በሰ ዓታት እንዲሁም በልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገ ልግሎት ጊዜ እየለበሱ እንዲሠሩ አድርጎአል ። ፈልና ጠብ እንዳይኖር ቀ ዋ ሚ የካህናት አስ ታራቂ ኰሚቴ በማቋቋም ሥራውን በተቀላ ጠፈ ይዞታ በመሥራት ላይ መሆኑን በተነበ በው ሪፖርት የገለጸው ሰበካ ጉባኤ የወደፊቱ ንም የሥራ ትልም ሳይጠቁም አላለፈም ። የክሊኒኩን ክፍሎችበመጨመር ፭ ክፍሎች አሠርቶወደ ፲፪ ማሳደግ ።



ቅዱስ ፓትርያርኩ ከሊቃነ ጳጳሳት ጋር በምረቃው ሥርዓት እንደተገኙ

- ከእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ጋር በመነጋገር ፰፻ ለሚሆኑ ድሆች ለሁለት ተከታታይ ጊዜ ያት የልብስ ርዳታ እንዲያገኙ ረድቷል ።
- ከቤተ ክርስቲያኑ በታች ባለው ትልቅ ወንዝ ዳር ለፈለቁት የቅዱስ እግዚአብሔር አብና የመድ ኃኔ ዓለም ጠበሎች መጠለያ ተሠርቶላቸው ለሕ ሙማን የጥምቀቱን አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ ።
- የካህናትን ደመወዝ በከፍተኛ ደረጃ በማሻ ሻል የሰንበት ት/ ቤት ተማሪዎችን ፍላጎት በመጠበቅ እንዲሁም በደብሩ ካህናት መከፋ ያለምንም አገልግሎት የሚገኘውን የውርስ ቤት አድሶና አሳምሮ በሥራ ላይ ማዋል
- በቂ የሆነ የስብከተ ወንጌል አዳራሽ ለማሠራት ከፍተኛ ፎቅ ሕንፃ ለማስጀመርና ምድር ቤቱን ለመቃብር ቦታ ማዋል ሲሆን የፕላኑም ሥራ
- የቅዱስ ገብርኤልን ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ በዘ መናዊ ፕላን ለማሠራት ታቅዶ ሲሆን የሚ ገባቦታ ታይቶ አመራር እንዲሰጠው ለጠቅ ላይ ቤተ ክህነት አመልክቶ መልሱን በመጠ ባበቅ ላይ የሚገኝ መሆኑን ገልጾአል ።
- በመጨረሻም የሰበካ ጉባኤው አባላት በፍቅረ

ተከታዩን በ፳፯ኛው ገጽ ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

## ቅዱስነታቸው በቀጨኔ መድኀኔ ዓለም . . . .

ከ፳፫ኛው ገጽ የዞረ

እግዚአብሔርና በፍቅረ ቢፅ ታንፀው የተጣለባቸውን ኃላፊነት በፍጹም ታማኝነትና በቆራጥነት ደከመን ሰለቸን ሳይሉ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር መስዋዕት በማድረግ ለውጤት በቅተዋል ።



መልአከ ገነት ምናሴ ዘለቀ የደብሩ አስተዳደሪ ንግግር ሲያደርጉ

በይበልጥም የሰበካ ጉባኤው ም/ሊቀ መንበር አቶ ኃይሌ መከታ ደክመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በየጊዜውና በየዕለቱ በደብሩ በመገኘት ከአባላቱ ጋር በመወያየት በህብረት በመሥራት ያሳዩት ፍሬ ቀላል አይደለም ። ግለሰቦች በሚችሉት አቅም እንዲረዱ አምባሳደሮች ጉብኝት እንዲያደርጉ በመጋበዝ ወሰን የሌለው ጥረት አድርገዋል ። ከኪሳቸው ገንዘብ በማውጣት መጋረጃ ጸናጽል መቋሚያ የመሳሰሉትን በማሟላት ለካህናቱ በሙሉ ጋቢ በመሸለም በማበረታታት ለቢር ሥራ የሚያገለግልጠረጴዛ ምርጥ ከሆኑ ፲፪ ኮምፕሌት ወንበሮች ጋር በገንዘባቸው ገዝተው በመስጠት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል ።

ይህ ሪፖርት ከደብሩ ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት ከቀረበ በኋላ ቅዱስነታቸው ሌሎች አድባራትና ገዳማት ይህንን አርአያ በማድረግ የገቢ ምንጭ እየፈጠሩ ራሳቸውን ከመርዳት አልፈው ለአካባቢው ምእመናን ጭምር እንዲረዱ ቢሆን የቤተ ክርስቲያናችን የአስተዳደር ዕድገት የካህናቱ ኑሮ በይበልጥ የሚሻሻል መሆኑን በማስረዳት መመሪያና ቡራኬ ሰጥተው የምረቃው ሥነ ሥርዓት በዓል ተፈጽሟል



ቅዱስነታቸውን መዘምራን በዝማሬ ሲቀበሉ

ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ከመልአከ ገነት ምናሴ ዘለቀ የደብሩ አስተዳዳሪ የተበረከቱ ቅኔዎች

ጉባኤ ቃና
ነዋ ተዐውቀ ደብረ ሰላም ከመ ዳግመ ተወልደ
ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስ እስመ በላዕሌሁ ወረደ
መወድስ
እፎኑ ተዓቢ እምካልዓኒሃ ኢትዮጵያ እምነ ምልዕተ ሰላም ወፍቅር
ወኢይትማሰላ መኑመ እምአንስተ ዙሉን አህጉር
እኮኑ በኢያጽርአ
ይውኅዝ እምከናፍሪሃ ጳውሎስ መዓር
ወዘልፈ ይሔውፃ
ለቤተ ክርስቲያን ጳውሎስ መልአከ ዘበምድር
ለዓለም
ንንግርሂ ወንዜኑ ዕበየ ጳውሎስ ኄር
እስመ ድኅረ ሞተ ያነሥእ ለመካነ ኮሌጅ አልዓዛር
ባሕቱ ጳውሎስ መዝገበ ጥበብ ወምክር
ለዘተሣሃለ ይሣሃል ወለዘመሐረ ይምሕር

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዓለም አቀፍ

ከ፲፱ኛው ገጽ የዞረ

የእስክንድርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ወክለው የተገኙት ፤

፩/ ብፁዕ አቡነ ቢሾይ የእስክንድርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ
፪/ ብፁዕ አቡነ ሲራኒዮን የውጭ ግንኙነትና የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ
፫/ ብፁዕ አቡነ ሙሳ የወጣቶች ጉዳይ ኃላፊ ፤
፬/ ብፁዕ አቡነ ማርቆስ በኬንያ የግብጽ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ናቸው ።

ብፁዕ አቡነ ደማስኪንኖስ በጀኔቫ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ደግሞ ለሁለት ቀናት ያህል በተመልካችነት በስብሰባው ላይ ተሳትፈዋል ።

ከዚህ ሌላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያላት ዓለም አቀፋዊ ግንኙነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመሄድ ላይ ይገኛል ።ይህም ይታወቅ ዘንድ የአልክስንድርያና የመላ አፍሪካ የግሪክ ኮሚኒቲ ፓትርያርክ አቡነ ፓትርኒዮስ ከሁለት ጳጳሳት ጋር ሆነው ለአንድ ሳምንት ያህል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሥራ ጉብኝት ለማድረግ መጋቢት ፲፩ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ/ም አዲስ አበባ ሲገቡ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትን አስከትለው በዚሁ ዕለት ከጥዋቱ ፫ሰዓት ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ በመገኘት አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ መጋቢት ፲፫ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ/ም ከጥዋቱ ፬ ሰዓት ገደማ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ፔትሪኒዮስን በጽሕፈት ቤታቸው ተቀብለው በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የቆየውን ግንኙነት አስመልክተው ሐሳብ ለሐሳብ ተወያይተዋል ። በተለይ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በምዕራቡ ክፍለ ዓለም ጣዖትን ያመልኩበት በነበረበት ወቅት በእውነተኛው አምላክ እንዲያመልኩ ያደረገችው የሃይማኖት አስተዋፅኦ ከፍተኛ እንደነበረ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ለብፁዕ አቡነ ፔትርኒዮስ የአልክሳንድሪያና የመላው አፍሪካ የግሪክ ኮሚኒቲ ፓትርያርክ አስረድተዋል ። በዚሁ አንጻርም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ከአበው የተቀበለችውን እምነትና ሥርዓት ጠብቃ በአፍሪካ ክፍለ ዓለም በቀዳሚነቷና በምሳሌነቷ የምትጠቀስ መሆኑን ገልጸዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ፔትርኒዮስ የአልክሳንድሪያና የመላው አፍሪካ የግሪክ ኮሚኒቲ ፓትርያርክ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን አቅም በፈቀደ መጠን የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እንደምትረዳ ለቅዱስነታቸው ቃል ገብተዋል ። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ፔትርኒዮስ በአዲስ አበባ ውስጥ ለሚገኙት ለግሪክ ኮሚኒቲ አባታዊ ምክር በሚለግሱበት ወቅት ኢትዮጵያውያንን ወንድሞቻቸው እነርሱም እኛን ግሪካውያንን ይወዱናል ። ሲሉ አረጋግጠዋል ።

የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ይህን የፍቅር ምልክት በተግባር በመግለጽ ላይ ትገኛለች ።

፩/ ለሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት
፪/ ለሰበታ ቤተ ጠባባት ደናግል ገዳም ፤
፫/ ለዝዋይ ካህናት ማሰልጠኛ ት/ቤት የእርዳታ እጆቿን በመዘርጋት ከአስፈላጊው ማቴሪያል ጋር የገንዘብ ስጦታ በመለገስ ለቤተ ክርስቲያናችን ከፍተኛ ምግባረሠናይ በመፈጸም ላይ ናት ። እንዲሁም በቅርብ ለሚከፈተው መንፈሳዊ ኮሌጅ ንብረትነቱ ለግሪክ ቤተ ክርስቲያን የሆነ አንድ መለስተኛ መኪና(አውቶቡስ) ለአገልግሎት የሚውል ለግሳለች ።

የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ለወደፊቱም ቢሆን ርዳታዋን እንደምትቀጥል ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ፔትርኒዮስ ለቅዱስነታቸው የተስፋ ቃል አብሥረዋል ።

በመጨረሻም ቅዱስነታቸው መጋቢት ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ/ም ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትን አስከትለው ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በመገኘት ብፁዕ ወቅዱስ ፔትርኒዮስን የአልክሳንድሪያና የመላው አፍሪካ የግሪክ ኮሚኒቲ.ፓትርያርክ አሸኛኘት አድርገውላቸዋል ።

ቀሲስ ኢያሱ ገብሬ
የውጭ ግንኙነት መምሪያ ኃላፊ

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ከ፲፭ኛው ገጽ የዞረ

እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? በማለት ጠያቃት ። ሔዋንም «አይደለም ፤ በገነት ካለው ዛፍ - ፍሬ ሁሉ እንበላለን ፤ ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ዕፀ በለስ ፍሬ እዳንበላ ፤ አዝዞናል ከዚያ የበላን እንደሆነ ግን እንደምንሞት ነግሮናል ፤ አስጠንቅቆናል አለችው ። በዚህ ጊዜ ዲያብሎስ» አኮ ሞተ ዘትመውቱ ፤ አላከመ አማልክት ትከውኑ ሞትን የምትሞቱ ሆኖ አይደለም ፤ ከዚህ ዛፍ ፍሬ በበላችሁ ጊዜ አይናችሁ እንደሚከፈትና ክፉውንና በጎውን ለይታችሁ እንደምታውቁ አምላክም እንደምትሆኑ እግዚአብሔር አውቆ ከለከላችሁ እንጂ አላት ። በዚህ ጊዜ ሔዋን ለመብ

ተከታዩን በ፳፯ኛው ገጽ ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ከ፩፭ኛው ገጽ የዞረ

ላትም ነመጀች ፡ ጥበበኛ ለመሆንም ጓጓች። ስለዚህም ቀነጠሰችና በላች ፤ ለባሏም አበላችው በዚህ ጊዜ ዕርቃናቸውን ወጡ በሐፍረት ተዋጡ ፤ የበለስን ቅጠል ቀረጡ በዚህ ቅጠል ሐፍረታቸውን ሸፈኑ እግዚአብሔር በገነት ሲመላለስ የኮቴውን ድምፅ ሰምተው ከአትክልት መካከል ተወሸቁ ። ዘፍ - ፫ ፩—፱

በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር አምላክ «እነሆ አዳም መልካሙንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ» በማለት አሁንም እጁን እንዳይዘረጋና ደግሞም ከሕይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ ፤ ለዘለዓለምም ሕያው ሁኖ እንዳይኖር ከኤደን ገነት አስወጣው ፤ የተገኘበትን መሬት ያርስ ዘንድም አዘዘው ። ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍን በኤደን ገነት ምሥራቅ አስቀመጠ ። ዘፍ - ፫-፳፪-፳፬ ።

ከላይ ከፍ ብሎ እንደተገለጸው ገነት ማለት ለዓይን የሚያስደስቱ ለምግብም የሚበጁ ፍሬያት የሚገኙበት ለምለም ቦታ ሲሆን አዳምና ሄዋን የፈጣሪያቸውን ትእዛዝ ጠብቀው ቢሆን ኑሮ በእነዚህ በታወቁት አራት ታላላቅ አፍላጋት በተከበበች በአበባና በፍሬ በተዋበች ገነት ውስጥ ለዘለዓለም ሕያዋን ሁነው ይኖሩ ነበር ፤ አልሆኑም ተባረሩ ፤ አሁንም በገዛ ሥልጣናቸው እጃቸውን እንዳይዘረጉና ከዕፀ ሕይወት እንዳይቀምሱ ከተባረሩ በኋላ መንገዱም የነበልባል ሰይፍ በያዙ መላእክት ታጠረባቸው ።

ከዚህ ቅዱስ መጽሐፍ እንደምንረዳው «እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ከገነት አስወጣው» ሲባል ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም እስከትመለስለት ድረስ ገነት የእሱ አለመሆንዋን ባለመሆንዋም እንደ ገና ተመልሶ በዚያች እጠቀማለሁ እንዳይል በአምላክ ፍርድ መከልከሉን ነው የምንገነዘበው ።

ስለዚህ እኛ ገነትን በገነትነትዋ በዓይነ ሥጋ ለመለየት ባንበቃ በአካባቢዋ እንዳለን ከቅዱስ መጽሐፍ የበለጠ ሌላ ማስረጃ ፍለጋ የምንባዝንበት ምክንያት አይኖረንም ዘፍ-፪-፲፫ ።

እኛ ኢትዮጵያውያን በገነት አካባቢ መሆናችንን የሚያስገነዝቡ ከተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ቁጥሮች የማይጋጩ ተመሳሳይነት ያላቸው ቁም ነገሮችን እናገኛለን ። ፩/ ከቅዱስ መጽሐፍ ስንወጣ ፤ ገነትን ከሚያጠጡ አራቱ አፍላጋት አንዱ ኢትዮጵያዊው ዓባይ መሆኑ አያከራክርም ። ይህ ዓባይ (ፈለገ ግዮን) ኢትዮጵያን የሚከብብ መሆኑም ከመጽሐፍ ጋር በአገረ ህሊና ብንጓዝና በዓይነ ህሊናም ብንመለከት በገነት አካባቢ መሆናችንን ለማረጋገጥ እንበቃለን ። ፪/ በዚህ በፈለገ ግዮን መውረጃ አካባቢ በጾም በጸሎት ተጠምደው ከዚህ ዓለም ሥራ ተወግደው ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጋገሩ የሚኖሩ ኀቡዓን መኖራቸውም ብዙዎች መንፈሳውያን አባቶች የሚያውቁት እውነት ነው ።

፫/ እንደአግራ ሳይንት ባሉ ብዙ የገነትን ምሥጢር የሚያሳዩ ተአምራት ይገኛሉ ፤ እነዚህም ፤ ሀ/ በአውሻሽ ሥላሴ አንድ የዋርካ ዛፍ በሁለት ታላላቅ ቅርንጫፎች የተከፈለ ሆኖ ማለት አንዱ ቅርንጫፍ በምሥራቅ ፤ ሌላው ቅርንጫፍ በምዕራብ በኩል ያመለክታሉ ። ታዲያ በምሥራቅ በኩል ያለው ቅርንጫፍ ወይን ሲያፈራ ፤ በምዕራብ በኩል የሚታየው ደግሞ ዋርካ ያፈራል ። በየዓመቱ ዋርካው ያፈራው ተለውጦ ወይን ሲያፈራ ፤ ወይን ያፈራው ደግሞ በዓመቱ ተለውጦ ዋርካ ያፈራል ። ይህንንም የዓይን ምሥክሮች ያረጋግጣሉ

ለ/ በደብረ እንድርያስ ደብረ ቀዘት አካባቢ አንድ ውሀ አለ ፤ የሰንበሴጥ ግር ጎንጉነው ከውሀው ቢያስገቡት መቋጠሪያ ሆኖ ይወጣል መናንያን ይጠቀሙበታል ።

፬/ በዋልድባ ፤ አብረንታንት በትግራይ በመዝባዕ ፤ በአፈ ጌትናበነጭ ግር የመሳሰሉ ገዳማት (በረሀዎች) የገነት ኑሮ የሚኖሩ ህቡአን አሉ ። እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ፤ እህል ውሀ ሳይቀምሱ ቅጠላ ቅጠልና የዛፍ ፍሬ በመቅመስ የሚኖሩ እጅግ ብዙዎች ናቸው ።

፭/ በትግራይ በዓድዋ አውራጃ በከተማው ከሚገኘው የቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የወይራ ዓጸዶች በየዓመቱ ማር ያዝንም ነበር ። በጎንደር እንደወገራ ማቋ ልክ ኢየሱስ የመሳሰሉት አካባቢ ማር የሚያዘንሙ አሉ ዋናው መልእክታችን በገነት ውስጥ ነው የምንገኘው ብለን እንድንኩራ ሳይሆን ከላይ እንደተመለከትነው አሁንም በዚህች ገነታችን ሁለቱ ዕፀዋት መኖራቸውን እንዳንዘነጋ ነው ። አባታችን አዳምና እናታችን ሔዋን በሕይወት ማኖር የሚያስችል ዕፅና የሚገድል ሌላ ተቃራኒ ዕፅ ተተክለውባቸው እንደነበር ሁሉ አሁንም ክፉንና በጎን ለይተን የምናውቅባቸው ዐሥሩ ቃላተ ኦሪትና ፯ቱ ቃላተ ወንጌል ሕያዋን ሁነን መኖር የሚያስችለን ሥጋውና ደሙ ተሰጥተውናል ። ትእዛዛቱን ከጣስን ዕፀ በለስን ቀንጠስን ፤ ትእዛዛቱን ጠብቀን በሥጋውና በደሙ ከተወሰንን ፤ ዕፀ ሕይወትን በልተን በሕይወት መኖርን መርጠናል ማለት ነው ።

ዕፀ ሕይወትን እንድንመርጥ ልቡናችንን ያብራልን



## . . . የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች ምስክርነት

ከ፩፪ኛው ገጽ የዞረ

እውነትነት ለማግኘት ሲሉ ክርስትናንና እስልምናን እያነጻጸሩ በማሳየት ጥያቄ አቀረቡ ። ጥያቄውም እንደዚህ የሚል ነው ።

፩ኛ/ የክርስትናን ሃይማኖት ስንመለከተው ቤተ ክርስቲያንን የመሠረታት ራሱ ክርስቶስ ነው ። ክርስቶስ ደግሞ ከመወለዱ በፊት ነቢያት የተነበዩለት መልአኩ ገብሪሊም ማርያም በድንግልና እንደምትወልደውና ስሙንም ኢየሱስ እንደምትለው በብሥራቱ የተናገረላት እሱ ክርስቶስ መሆኑን የዓለም ታሪክም እንኳ ቢሆን የሚመሰክርብን ስለሆነ ልናስተባብለው አንችልም እንዲሁም ሞቶ ከተቀበረ በኋላ ሞትን አሸንፎ የተነሣና ያረገ ጌታ ነው የእኛ የሃይማኖት መሪ መሐመድ ግን እንዲሁ ነቢይ እንለዋለን እንጂ ከመወለዱ በፊት አንድም ነቢይ ወይም መልአክ ስለ እርሱ የመሰከረለት የለም ከሞተ በኋላም ሞትን ማሸነፍ አልቻለም ።

፪ኛ/ በሥነ ምግባር በኩል ሲታይም የእኛ ሃይማኖት ሰውን ሰው እንዲገድለው ያዝዛል ይህ ድንጋጌ ከእውነት አንጻር ሲገመገም አላህ እንዲህ ዓይነቱን ሥርዓት ያዝዛል ብለን ለማ መን አስቸጋሪ ነው ። ክርስቲያኖች አክብረው በያዙት በኦሪት ሕግና አሁንም በሐዲስ ኪዳን በአጠቃላይ በሃይማኖታቸው ሰውን ሰው መግደል ኃጢአት ነው እኛም ይህ ሁኔታ እውነተኛ አምላካዊ ትእዛዝ መሆኑን መጠራጠር የሚያስፈልግ አይመስለኝም ።

፫ኛ/ የሰው ልጅ መራባትና መባዛት እንዲችል አላህ አክብሮ የፈጠረውን ጋብቻን ክርስቲያኖች ክቡር ቅዱስ ጋብቻ ብለው አክብረው ይጠብቁታል ። ጋብቻ በማኅበራዊ ኑሮ በኩልም ዋነኛ መሠረት ስለሆነ ሊከበርና ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ ሲሆን የእኛ የሃይማኖታችን የጋብቻ ሕግ ግን አንድ ለአንድ በማለት ፈንታ አንድ ለብዙ ነው የሚለው በዚህ የተነሣ ሰዎች በፈጣሪያቸው ዘንድ እኩል ክብር ያላቸው መሆኑ በሚያጠራጥር መንገድ ብዙ ሴቶች እንደ ዕቃ በአንድ ወንድ ቤት እንዲጠራቀሙ ማድረግ የሴቶችን ክብር መገፈፍ ከመሆኑም በላይ አንድ ሰው ከብዙ ሰዎች ጋር መተኛት ማለት ለሕይወትና ለማኅበራዊ ኑሮ ጠንቅ ነው በማኅበረ ሰብ የማይወደድን ዝሙትንም ማስፋፋት ነው። ስለዚህም ይ ህ ሃይማኖታዊ ሥራ ነውለማለት እጅግ አስቸጋሪ ነው ብለው አስምረውበታል ።

፬ኛ/ ኦሪት ነቢያት ነበሩ እውነትም ናቸው ብለን እናምናለን መጽሐፎቹ ግን በድርጅታችን የሉም በክርስቲያኖቹ እጅ ያሉትን ደግሞ ተበርዘዋል ተከልሰዋል እንላለን ይህም የመጨነቅ የመቸገር ጉዳይ ካልሆነ በቀር ምንም የእውነትነት ምልክት የለውም በማለት ጥያቄአቸውን አጠናቅረው አቀረቡና ሃይማኖቱን እውነት ነው ብለን መቀበል እንድንችል ትክክለኛ መልስ ስጡን ያለዚያ ብለው ቀጥሎ ያለውን ዓረፍተነገርሳይዘጉ-ቃላቱን ቋጭተው አቆሙት ። በእውነቱ ይህ ቃል ከልብ ለሚመለከተው ሰው እነዚህ ጥያቄዎች መልስ ካላገኙ ወደ ክርስትና እምነት ለመግባት የተዘጋጁ መሆናቸው አያጠራጥርም ። ለዚህ ጥያቄ መልስ ስላላገኙ በላብ ስለተዋጡ ካሉት ከሁለቱ ኪሶቻቸው ሁለት መሐርብ አውጥተው ፊታቸውን ለማድረቅ ቢሞክሩም መልሱ ከመጥፋት ሳቡ ከመመንጨት አልዳነም በአጠቃላይመልሱ እስካ ሁንም አልተገኘም ጥያቄው ግን ወደ ሌሎች ወጣቶች እየተዛመተ ነው ይላሉ ። ይህ ሊሆን የቻለው በቢላል መጽሔት መነሻ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች የሰጡት መሠረት ያለው ትምህርት ስለሆነ እውነትም ሰንበት ት/ቤት ለሃማኖታችን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው እንላለን ። ወጣቶችም የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት በሚገባ ተምራችኋል ገንዛቤ ወስዳችኋል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለሙ እየተመላለሰ በሚያስተምርበት ጊዜ «በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታሁ» ማቴ - ፲ ቁ ፴፪ ብሎ የተናገረውን ቅዱስ ቃል የፈጸማችሁና መልካም ሥራ የሠራችሁ በመሆኑ በዚሁ በርቱበት እንላለን ።

ደጉ ይትባረክ

## እናቶች ለልጆቻቸው

ከ፲፱ኛው ገጽ የዞረ

ቻው የመንፈሳዊ ዕድገት ግስጋሴአቸውን ገትቶታል ። ከዚህም የተነሣ ልጆቻቸው ለኅብረተሰቡ ሰላም ጠንቅ ለማኅበራዊ አገልግሎትም እንቅፋት በመሆን ለችግር ተዳርገዋል ። የዕለት ከዕለት ሕይወታቸውም እንዲሁ መራራ እየሆነ መጥቷል ።

ከእምነት ጋር ግንኙነት በሌለው መልኩ በከፍተኛ ፍጥነት እየጨመረ የመጣውን የምግባረ ብልሹ ልጆች ጠባይ ለማስተካከል ከቤተ ክርስቲያን የሥነ ምግባር ትምህርት ጋር ማስተዋወቅ ፍቱን መድኃኒት ይሆናል ። አባትንና እናትን ማክበር አብሮ ካደገ እግዚአብሔርን ከመፍራት ጋር ተያይዞ የሚገኝ ስለሆነ ይጠቅማል ።

«በአረጋውያን ፊት ተነሣ ሽማግሌውንም አክብር አምላክህንም ፍራ እኔ እግዚአብሔር ነኝ» ዘሌ ፲፱ ፥ ፴፪ ይህ ሣይሆን እየቀረ ብዙ ልጆች ተጎድተዋል ይህን በማረጋገጥ የእግዚአብሔር ቃል

ተከታዩን በ፴ኛው ገጽ ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

# ጥንታዊና ብሔራዊ የኢትዮጵያ ትምህርት

ከ፲፫ኛው ገጽ የዞረ

ጸፈ ሰማይ ጽፎ አሳይቶ ወዲያው በልቡ እየሳለ ፣ ሥነ ፍጥረትን አሥርቱ ቃላትን በቃል በፊደል ያስተምራቸው ዘንድ ያስፈውም ታሪክና ዜና ተረስቶና ተዘንግቶ እንዳይቀር ለቅሞ ሰብስቦ ይጽፍላቸው ዘንድ ሥራውንና አሠራሩን ሁሉ ጽፎ አሳይቶታል እየተባለ ይተረካል ፊደላትም በስማቸውና በቁጥራቸው የፈጣሪና የፍጥረት ምሳሌ እንደሆኑ ምሥጢራቸውን አስረድቶ የጽሕፈትና የትምህርት መሠረት አድርጓቸዋል ።

የፈጣሪና የፍጥረት ምሳሌ አድርጎ ማስረዳቱንም የምናውቀው የአዳምን ተስፋ ዳግማይ አዳምን በአርአያ ፊደል ሥሎ መስሎ ስሙንም "አሌፍ ታው" ብሎ በማሳየቱ ነው ።

ነቢያት ይልቁንም ዳዊት ፣ ኤርምያስ ፣ አቡቀለምሲስ ርሱን መስለውና ተከትለው ከባለቤቱም አፍ ተቀብለው ፊደላዊ ስሙን በፊደል ሰብከዋል ። የግሪክ ፊደል በእልፋ ጀምሮ በኦሜጋ ስለሚጨርስ ቀድሞ ለሄኖስ "አነ ውእቱ አሌፍ ወታው' ያለውን ኋላ ለዮሐንስ" አልፋ ወዖ" ብሎ መድገሙ የራእያቸውን አንድነት ያሳያል ። ተቀባዩና ሠራተኛው ሄኖስ ብቻ ሲሆን የፊደላት መገለጥና መስጠት በዘመናቸው ስለሆነ ይህን የሄኖስን ሥራ ገድለ አዳም ለአዳም ብቻ ፣ ፈላስፋው ቀሪጦን ለሴት ብቻ ሰጥቶ ይተርካል ። ባለቤትነት ግን ከሄኖስ አይወጣም ይላሉ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሰዋስው ወግሥ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ በተባለው መጽሐፋቸው (ከገጽ ፳፱—፳፬ ተመልከት ።)

ከሄኖስ እስከ ኖኅ ተያይዞና ተከታትሎ ለሚመጣው ትውልድ ሁሉ በሰሌዳ ዕብን እየተጻፈና በቤተ መዛግብት እየተቀመጠ መተላለፉን የአይሁድ ኩፋሌ በዕብራይስጥ ቋንቋ ይተርካል ።

በዚህም በሄኖስ ሥራ ዲያብሎስ ቀንቶ ተመቅኝቶ ጥሩውን ትምህርት ለማደፍረስ ራንሙ የሚባለውን ፬ኛ የአጋንንት አለቃ ጸሐፊ አድርጎ ከእግዚአብሔር በተገኘው ፊደልና ስነ ጽሕፈት ላይ በጠላትነት አስነሥቷል ።

ራንሙም ከእግዚአብሔር በተገኘው በቅዱስ ፊደል ሌላ ርኩስ ትምህርት ጥንቆላና ሟርት ስመ አጋንንት እንዲጽፉና እንዲያጽፉ እንዲያነቡም ፣ ያስተምራቸው ዘንድ በምትሀቱ ቀለምና ክርታስ በእጁ ይዞ ርኩስ ትምህርቱን እየጻፈና ጠልሰም እየሠራ መጽሐፍ አድርጎ አሳይቷቸዋል ይላሉታሪኩ ራንሙ እንደ ባለቅኔ እያሾከሾከ ምሥጢሩን ሁሉ በጆሮዋቸውና በዓይናቸው አጥግቦዋቸዋል ። ይልቁንም የደቂቀ ቃየን አለቆች እነ ስማዝያን ማሩን አምርር ፣ ወተቱን አጥቁር በመንገርና በማሳየት እንደ እናታቸው እንደሔዋን እያስጐመጀ ማርኳቸዋል ። ዛሬም የርሱን ሥራ ተከትለው በቅዱስ መጽሐፍ በዳዊት በወንጌል ፣ በጉልቂ ፊደል የሚያሟርቱ ፣ ርሱንም በገዛ አስማቱ የሚጎትቱ ፣ ለዲያብሎስም መልክ ደርሰው ጠላታቸውን ለመጉዳት በዳዊት ፈንታ መልኩን የሚደግሙ የስብእ ትካት ቁራጮች አሉ ።

ይህም ታሪክ እውነት ለመሆኑ ቀጥሎ ያለው የመጽሐፈ ሔኖክ ንባብ ያረጋግጥልናል ። "ወራብዕ ስሙ ራንሙ ፣ ዝ ውእቱ ዘአርአየ ለውሉደ ሰብእ መሪረ ወመዓርዒረ ! ወአርአዮሙ ኵሎ ኅቡዓተ ጥበቦሙ ለአጋንንት ወአለበዎሙ ውእቱ ለሰብእ መጽሐፈ በማየ ሕመት ወበክርታስ ። ወበእንተዝ ብዙኃን ይስሕቱ እምዓለም ወእስከ ለዓለም ወእስከ ዛቲ ዕለት እስመ ኢተወልደ ሰብእ ለዘከመዝ ግብር ከመ ያጽንኡ ሃይማኖቶሙ በቀለም ወበረቅ ፣ እስመ ኢተፈጥረ ሰብእ ዘእንበለ ከመ መላእክት ከመ ይኩኑ ጻድቃነ ወንጹሐነ ወሞት ዘኵሎ ያማስን እምኢገሠሦሙ ፣ አላ በዝ አዕምሮቶሙ ይትሁጐሉ ወበእንተዝ ይበልዐኒ ኃይል ሔኖ ፲፱ ፣ ፳፪—፳፭ ትርጉሙ በአማርኛውም ስሙ ራንሙ ይባላል ። ለሰው ልጆችም የጣፈጠውንና የመረረውን ያስተማረ ይህ ነው ።

የተሠወረ ጥበባቸውን አጋንንቱን ሁሉ አስተማራቸው ለሰዎችም በጥቁር ቀለም በወረቀት ቀይ መጽሐፍ መጻፍን አስተማራቸው ።

እንደ መላእክት ንጹሐን ጻድቃን ሁነው ይኖሩ ዘንድ ነው እንጂ ሰው በእንዲህ ያለ ሥራ አልተፈጠረም ። በጥቍር ቀለምና በቀይ ቀለም ጽፈውሃይማኖታቸውን ሊያጠኑ ሰው ለእንዲህ ያለ ሥራ አልተፈጠረም ነበርና ። ስለዚህ ነገር ከጥንት ጀምሮ እስከ ዘለዓለሙ እስከዚያችም ቀን ድረስ ብዙ ሰዎች ይስታሉ አለ ።

ይህን በማወቃቸው ይጠፋሉ እንጂ ሁሉን የሚያጠፋ ባላገኛቸውም ነበር" ማለት ነው ።

ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታየ
የትምህርትና ማሠልጠኛ መምሪያ ኃላፊ



# የሊቁ ክ/ ዮሐንስ

ከ፩ኛው ገጽ የዞረ

ቀውስጦስ ቤት እንኳን ሳይገባ ተመልሶ ከበአቱ ይገኛል ።

፱ኛ/ የሚገኘው በምሕላ ጊዜ ነው ከአደባባይ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ጃን ተክል የሚባል የሕዝብ መሰብሰቢያ አደባባይ አለ በየወሩ ከልደታ እስከሥላሴ ለ፮ ቀን ዓቢይ ምሕላ ይደረስበታል እንደ ሕጉ እንደ ስርዓቱ ሕዝቡ ከ፲፪ ሰዓት ጀምሮ ይሰበሰባል ።

እጨጌውም ከካህናቱ ንጉሡ ከመኳንንቱ ጋር በጃን ተክል ለምህላው ይገኛሉ ። ጸሎቱ የሚጀመር በ፩ ሰዓት ነው የሚፈጸመው በ፫ ሰዓት ነው በዚያን ጊዜ ህዝቡ የፈጸመውን በደል እያስታወሰ በፍጹም ልቡናው እያለቀሰ መሪር እንባውን እያፈሰሰ ፈጣሪውን በንስሐ ይቅርታን የሚጠይቅበት ጊዜ ይሆናል ከ፮ ቀን በኋላ ፤ ምህላው ሲፈጸም ለህዝቡ ተስፋ የሚሆን ብዙ ግቢረ ተአምራት ይደረጋል የተለያየ ምልክት ይታያል በከተማውም ተላላፊ በሽታ ገብቶ እንደሆነ ሌላም ደዌ ያለ ከሆነ ይታገሣል ፈጽሞ ይጠፋል በዘመኑ ድርቅ ሆኖ እንደሆነ ዝናመ ምህረት ይወርዳል ቀድሞ በኢ/ቤተ ክርስቲያን ለምዕመናን ከአበው ሊቃውንት በ፱ አርስት የተወሰነ በአመት የምህላ ጊዜ አለ በጃን ተክል የሚደረሰው ምህላ ከዚያ የሚቆጠር ነው ።

፲ኛ/ ሊቁ ጽርሐ ጽዮን ወደ ተባለችው ወደ ጻድቁ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት የሚሄድበት ጊዜ አለ እርሷም ፩፻፳ መምህራን እንደ አንድ ቤተሰብ ሆነው የሚኖሩባት የፍቅር ግንብ ናት ደቂቀ ኤዎስጣቴዎስ የቅባት ልጆችና ደቂቀ ተ/ሃይማኖት የተዋሕዶ ልጆች በየጊዜው የሚያነሱት የሃይማኖት ክርክር ነበር ስለዚህ ጉዳይ ለክፍለ ዮሐንስ ከእጨጌ በትረ ጊዮርጊስ ትፈለጋለህ የሚል መልእክት ይደርሰውና ይመጣል የተጠራበትም ነገር ይገለጽለትና ሁለቱም የሚለያዩበትን ጠባብ መንገድ ከመነሻም እስከ መድረሻው የሚያውቀው እርሱ ስለሆነ ከመጽሐፈ ሊቃውንትና ከሃይማኖተ አበው አንቀጽ እየጠቀሰ በማስረዳት ሁሉም መለያየትን አስወግደው የሚያዛልቃቸውን እውነተኛውን መንገድ ይዘው አንድ አካል አንድ ባህርይ በማለት እውነተኛይቱን ሀገ ወንጌል እያስተማሩ እንዲኖሩ ይመክራቸዋል ያስተምራቸዋል አይሆንም እንከራከራለን ካሉ ግን የጉባኤ ጊዜ እንዲወስንላቸውና አፈ ጉባኤ መርጠው እንዲነጋገሩ ሲል የመነጋገሪያውን ነጥብ ቃል ከራሱ አስተያየት ጋር ጽፎ ለእጨጌው አቅርቦ ለማስተማር ወደ ጉባኤው ይመለሳል ይኸውም በአፅንኦ በዓት ተወስና መኖርና መንፈሳዊ ትምህርትን ማስተማር ለመምህራን ተስፋ መንግሥተ ሰማያትን የሚያስገኝላቸው ተቀዳሚ ዕድል እንደሆነ ዜና ሊቃውንት ይናገራል አንቀጽ ፭ ፻ተኛ ዓምድ ከዚህ በኋላ ከዕለታት በአንድ ቀን አጼ ኢያሱ አድያም ሰገድ ደብረ ብርሃን ሥላሴ ሄደው ጸሎታቸውን አድርሰው ሲመለሱ ክ/ዮሐንስ ከወይራው ስር ተቀምጦ ሳይነሳላቸው ቀረ መኳንንቱም ባለመነሳቱ ደንግጠው ካህናቱ መቼም ይመቀኙታልና እያችሁን ብያ ይህ ትዒተኛ ንጉሡን ንቋቸው ሳይነሳላቸው ቀረ እያሉ የተቃውሞ ድምጽ አሰሙ አጼ ኢያሱ ግን ለክፋት እንዳላደረገው ያውቃሉና ተቃውሟቸውን አልሰሙአቸውም ይልቁንም ወደርሱ ቀረብ ብለው በሉሚ አምሳል መጠን የተቀረጸ የወርቅ እንክብል አውጥተው ደረቱን አሉት እርሱም ደንግጦ እንደ መፍከር ብሎ ቆመና «በእስጢፋኖስ አዕባን እመ ይሄልቁ ዘበጠኒ ኢያሱ በወርቁ» ብሎ የቅኔ መልስ ሰጠ ትርጓሜው ድንጋዮች በእስጢፋኖስ ቢያልቁ ኢያሱ መታኝ በወርቁ ማለት ነው በዚሕን ጊዜ የሕብረ ምስጢሩ ፈጥኖ መገኘት የኃይለ ቃሉ ብርታት ያስገረማቸው የሊቃውንቱ የመኳንንቱ ሳቅና ውካታ ይበል በሚል ድምጽ ሲያስተገባ ቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ ተንዶ የወደቀብን መስሎአቸው ሽሽት የጀሙሩ ብዙ ሰዎች ነበሩ ይባላል ክ/ዮሐንስም የተመታበትን ወርቅ አንስቶ ይዞ ለንጉሡ በቅኔ ብዙ ምስጋና ካቀረበ በኋላ ከእርሳቸው አስፈቅዶ የተሰጠውን ወርቅ በመልአከ ብርሃናት ቀወስጦስ እጅ ለደብረ ብርሃን ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ገቢ አድርጎታል ይኸውም ወርቅን ያህል ሀብት በመናቅ ያሳየው መንና ጥሪት ለእርሱ ፍጹም ባሕታዊ መናኔ አለም መሆኑን አስረድቶለታል ። ቅኔውም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ሊቁ ክ/ዮሐንስ እንዲህ አለ እየተባለ በጎንደር የሕጻናቱ አፍ መፍቻ የሽግግሌዎቹ መጽሐፋዊ ተረት መተረቻ ለሊቃውንቱ የተሰወረ ቅኔ መግለጫ ሆኖ የአጼ ኢያሱን ደግነትና የክ/ዮሐንስን ሊቅነት እያስታወሰ በመዘከርነቱ ጸንቶ ይኖራል እንግዲህ የዚህ ጽሑፍ ማጠቃለያ የሚያሳስበን ሁሉን ከታሪክ መማር እንደሚገባ ነው ሊቁ ነገሥታቱ የሚሰጡትን ወርቅና ብር የከበረ ሽልማት እርግፍ አድርጎ ትቶ ፍቅረ ንዋይን ድል ነስቶ ከዕለትምግቡ እንኳን ሳይቀር ለድሆች እያካፈለ በማስተማር በምናኔ ጊዜውን ያሳለፈው ዓለምና በዓለም ውስጥ ያለውን አትውደዱ ሀብቱም ንብረቱም ሁሉ ኃላፊ ነው ያለውን የሐዋርያውን ቃል በማሰብ ነው እንዲህ ከሆነ እኛም በፍቅረ ንዋይ ተጠምደን ከኃላፊው ዓለም ጋር ስንተናነቅ የማያልፈው ዓለም የእግዚአብሔር መንግሥት እንዳይቀርብን እንጠንቀቅ በአምላካችንም ዙፋን ፊት በቆምን ጊዜ በቸርነቱ የሚሰጠንን ፍጹም ሰማያዊ ሀብትን ለመቀበል የበቃን ሁነን እንገኝ ዘንድ ፈቃድህ ይሁንልን እያልን እንለምነው በማለት ያለብኝን የታሪክ እዳ ለቤተ ክርስቲያን ልጆች አስተላልፋለሁ ።

አለቃ ኤልያስ ነቢየ ልዑል



www.ethiopianorthodox.org

# እናቶች ለልጆቻቸው

ከ፳፯ኛው ገጽ የዞረ

እንዲህ ይላል «አባቱን ወይም እናቱን የሚሰድብ ሰው ቢኖር የኩርሱ መብራት በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ይጠፋበታል ።» ምሳሌ ፳ ፣ ፳ ስለዚህ ልጆች በመንፈሳዊ አስተዳደግ በፈሪሃ እግዚአብሔር ሊያድጉና ሊመላለሱ ይገባል ።

በአሁኑ ጊዜ ያሉ እናቶች ምክራቸውና ተግሳጻቸው ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ በመልካም አርአያነታቸው የተጠቀሱ ወላጆችን የተከተለ ሊሆን ይገባል ፤ በእግዚአብሔር ሕግ የሚያሳድጉ እናቶች እንደመሆናቸውም መጠን የእግዚአብሔርን ቃሉን እንዲያጠኑ መልካም ምግባር እንዲማሩ ዕለት ዕለትም ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲያነቡ የጥሩ ወጣቶችንም አርአያነት በተለይ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንዲረዱ ማድረግ ይፈለግባቸዋል ።

በመጽሐፈ ሳሙኤል ፩ ፤ ፳፩ ታሪኳ የተጠቀሰው ሐና እመ ሳሙኤል ከእግዚአብሔር የብፅዓት ልጅ በአገኘች ጊዜ ስሙን ሳሙኤል ብላ ጠራችው። ጡት መጥባት እስኪተው ድረስ አብራ አሳደገችው በኋላም ታማኝ አገልጋይ እንዲሆን ለቤተ እግዚአብሔር ሰጠችው ከሕጻንነቱ ጀምሮ ስለእግዚአብሔር አስተምራው ስለነበር በታማኝነት ፈጣሪውንና ሕዝቡን አገለገለ ለእግዚአብሔር ታዛዥ እንዲሆን የተሰጠ መሆኑንም ደጋግማ አስጠናችው ደጋግማ ትጸልይለትም ነበር ። በመጨረሻም በእግዚአብሔር ቤት ስለአደገ ታላቅ ነቢይ ለመሆን በቃ ።

ለመላው እሥራኤል መንፈሳዊ መሪ እንዲሆን እግዚአብሔር መረጠው ለሕዝቡም የፈጣሪውን መንገድ እያሳየ እየጸለየም ከኃጢአታቸው መልሷቸዋል ።

እናቱ ሐናም ሳሙኤልን የመሰለ ነቢይ በማግኘቷና በማሳደጓ ክብርን ተቀዳጅታለች ።

በሐዋ ሥራ ፲፮ ፤ ፩—፫ እንደምናነበው ቅዱስ ጳውሎስበማስተማር ዘመኑ አንዲት ሴት ልጅዋን ለደቀ መዝሙርነት ያስለፈችበትን ምዕራፍ እናገኛለን ። «ወደ ደርቤንና ልሥጥራንም ደረሰ ። እነሆም በዚያ የአንዲት የአመነች አይሁዳዊት ልጅ ጢሞቴዎስ የሚባል አንድ ደቀ መዝሙር ነበረ ። አባቱ ግን የግሪክ ሰው ነበረ ለእርሱም በልስጥራና በኢቆንዮን ያሉ ወንድሞች መሰከሩለት ። ጳውሎስ ይህ ከእርሱ ጋር ይወጣ ዘንድ ወደደ ።

የተጠቀሰችይቱ ሴት ከባሏ ጋር በክርስቶስ ካመነችበት ጊዜ ጀምሮ ሕይወቷ ተለወጠ ። መንፈሳዊ አገልግሎቷንም እየፈጸመች ሳለ ልጅ ወለደች ። ስሙንም ጢሞቴዎስ ብላ አወጣችለት ። አካሄዱም አስተዳደጉም በሥርዓት እንዲሆን በመፈለጓ ከሕፃንነቱ ወራት ጀምራ እዘውትራ ወደጸሎት ቤት ትወስደው ነበር ምኞቷም ሐሳቧም እድገቱ በቤተ ክርስቲያን እንዲሆን ስለነበረ የተቻላትን ሁሉ ያለ መሰልቸት ፈጽማለታለች ። ሕይወቱ በጥሩ ሥነ ምግባር የተመሠረተው ጢሞቴዎስ ታዛዥነቱ ፤ ተግባቢነቱና ሰው አክባሪነቱ የእግዚአብሔርና የሰው ፍቅር አደረበት ።

ከላይ እንደተጠቀሰው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ደርቤን መጣ ። በዚያም እርፎ ሳለ ኤውንቄ የክርስቶስን ቅዱስ ቃል እንዲያስተምር በተግሳጽም እንዲያሳድግለት ልጅዋን ጢሞቴዎስን ሰጠችው ። ሐዋርያውም የኤውንቄን እምነትና ጥንካሬ ተመልክቶ አመሰገናት እደነቃትም ልጅዋንም በፍጹም ደስታ ተቀበላት ። በዚያም የነበሩ ወንድሞች ሁሉ ጢሞቴዎስን እናቱ በመልካም አስተዳደግ ያሳደገችው ጠባዩ የቀና መንፈሳዊ መሆኑን እያንዳንዳቸው እየቀረቡ መሰከሩለት ። ሐዋርያው በሰማው ሁሉ እጅግ ተደስቶ ጢሞቴዎስን ፤ እስከ ትሎ ይዞት ሄደ ።

ከዚያን ቀን ጀምሮ ሐዋርያ ማለት ተግባሩ ምን እንደሆነ እየተነተነ አስተማረው ። ስለ ወንጌል መስፋፋት ስለምእመናን ብዛት አቅሙ በሚችለው ሁሉ እንዲጥር መንገዱን አሳየው።በሐዋርያው ትምህርት ጢሞቴዎስ ልቡ ስለተነካ የሚለውን ሁሉ ይሰማውና ይፈጽመው ነበር ።

በዚህ ድንቅ ተግባሩ የተደሰተው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ኤጲስ ቆጶስነት ሾሞ ላከው ጢሞቴዎስም ተሾሞ በሄደበት አገር የክርስቶስን ቃል እያስተማረ በልጅና በእናት በባልና በሚስት መካከል ሊኖር ስለሚገባው ፍቅርና መከባበር እያስተማረና እየመከረ ኖሯል ። ስለቤተ ክርስቲያን እድገትና ልማት ለክርስቲያኖችም ቁጥር መጨመር ያልተቆጠበ ጥረቱን ያደረገ ቸር ጠባቂ ሆነ ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም መንፈሳዊ ጀግንነቱን ሲሰማ በጣም ተደሰተ ። ይህንንም ጥንካሬ ሊያገኝ የቻለው በመንፈሳዊት እናቱና አያቱም ጭምር መሆኑን በመገንዘብ እንዲህ እያለ አመስግኖ ከሰላምታ ጋር ጽፎለታል ።

በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የሆነ ጳውሎስ ለተወደደው ልጄ ለጢሞቴዎስ ከእግዚአብሔር አብ ከጌታችንም ከኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋና ምህረት ሰላምም ይሁን ሌትና ቀን በልመናዬ ሳላቋርጥ ስለምናገር እንደአባቶቼ አድርጌ በንጹህ ህሊና የማመልከውን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ ። እንባህን እያሰብሁ በደስታ እሞላ ዘንድ ላይህ እናፍቃለሁ ። በአንተ ያለውን ግብዝነት የሌለበትን እምነትህን አስባለሁ ። ይህም እምነት ቀድሞ በአያትህ በሎይድ በእናትህም በኤውንቄ ነበራቸው ። ስለዚህ ምክ በአንተም ደግሞ እንዳለ ተረድቻለሁ ። ስለዚህ ምክ

ተከታዩን በ፴፩ኛው ገጽ ይመልከቱ



# የሰበካ ጉባኤ ዓላማና ተግባር

ከ፲፰ ገጽ የዞረ

በሐዋርያት ጊዜ በሐዋርያት ጉባኤ ተመክሮና ተወስኖ በተላለፈው ሕግና ሥርዓት በማኅበረ ምእመናኑ ጠቅላላ ጉባኤ በተመረጡ ቅዱስ መንፈስ ባደረባቸው ሰዎች ይካሄድ እንደ ነበር (ግብረ ሐዋ ፣ ምዕ ፣ ፮ ፣ ፩—፮)ይገልጻል ፣ ሀብቷና ንብረቷም ከምእመናን በአስተዋጽኦ ተሰብስቦ ለአገልጋዮቿ መተዳደሪያ ፣ ለሐዋርያዊ ሥራ ማስኬያጃና ለችግረኞች መርጃ እንዲውል ይደረግ እንደነበር (ግብረ ሐዋ ፡ ምዕ ፲፩፣ ፴፱ ፣ ምዕ ፣ ፳ ፣ ፲፩ ። ፩ኛ ፡ ቆሮ ፡ ምዕ ፡ ፲፮ ፣ ፮—፲፩) በቤተ ክርስቲያን በታሪክና በቅዱሳት መጻሕፍት በግልጽ ተመልክቷል ።

፱/ በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ዓላማና ተግባርም ከዚህ ሌላ መሆን ስለማይኖርበት ፣

፩/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች ምእመናን በሃይማኖት እንዲፀኑ በመንፈሳዊ ዕውቀት እንዲጎለምሱና በስነ ምግባር እንዲታነጹ ።

፪/ ስብከተ ወንጌል እንዲጠናከር ፣

፫/ ጥንታዊውና ነባሩ የቤተ ክርስቲያንመፈሳዊ ትምህርት መሠረታዊ ይዘቱ ሳይፋለስ በየደረጃው እንዲጠናከርና የቤተ ክርስቲያን አዕማድ ለሆኑት ሊቃውንትና መምህራን ተገቢው እንክብካቤ እንዲደረግ ፤

፬/ ካህናት ለምእመናን የሚያበረክቱት መንፈሳዊ አገልግሎትና ምእመናንም ለቤተ ክርስቲያን ሊያደርጉት የሚገባቸው አስተዋፅኦ የተሟላ እንዲሆን ለማድረግ ፤

፭/ ከምእመናን በሚገኘው አስተዋጽኦ የካህናትን ኑሮ ለማሻሻል ፣

፮/ እያንዳንዱ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የወደፊቱን የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና ተተኪዎች የማዘጋጀት ኃላፊነት ስለአለበት የሰንበት ትምህርት ቤትን በእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋምና ለማጠናከር ፣

፯/ በሰበካ ጉባኤያት አማካይነት ተግባረዕድን ለማስፋፋትና በውጤቱም የተሟላ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎትን ለማበርከት የሚረዳ የገቢ ምንጭ ለመፍጠር ፣

፰/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ ምስካየ ኅዙናን መጽንኤ ድኩማን እንደመሆንዋ አሁንም በእያንዳንዱ የአጥቢያ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ እጓለ ማውታ ሕፃናት በእንክብካቤ የሚያድጉበት ፣ ሽማግሌዎች የሚጦሩበትና ችግረኞች የሚረዱበት የምግባረ ሠናይ ድርጅት እንዲኖር ፣

፱/ የቤተ ክርስቲያን ገንዘብና ንብረት እንዲሁም ታሪካዊነትና ጥንታዊነት ያላቸው ቅርሶች በጥንቃቄ እንዲጠበቁና አያያዛቸውም ዘመናዊ እቅድ እንዲኖረው ለማድረግ ፣

፲/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ካህናትና ሠራተኞች ሁሉ እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ሠራተኛ መብታቸው የተጠበቀ ይሆን ዘንድ የጡረታ አስተዋጽኦ መክፈልና የጡረታ አበል ማግኘት እንዲችሉ ፣

፲፩/ በአጠቃላይ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እስከ ወረዳ ከወረዳም በየደረጃው እስከ ሀገረ ስብከት ፣ ከሀገረ ስብከት እስከ መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ድረስ ሰበካ ጉባኤን ደረጃ በደረጃ በማቋቋም የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር በማዕከላዊ አመራር ለማጠናከር ይቻል ዘንድ ቅዱስ ሲኖዶስ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር ፫፻፺፰ እና ፫፻፺፱ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በተሰጠው መብት መሠረት የተሻሻለውን የቃለ ዓዋዲ ደንብ አውጥቷል ።

መሪጌታ ተአምር ገ/መስቀል የሰበካ ጉባኤ ማደራጃ ዋና መምሪያ ዋና ጸሐፊ

# እናቶች ለልጆቻቸው

ከ፴ኛው ገጽ የዞረ

ንያት እሳት እንደሚያቀጣጥል ሰው እጆቼን በመጫን መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልተሰጠንምና ፤ በማለት የማበረታታት ምክር ሰጥቶታል ። (፩ኛ ጢሞ ፩ ፤ ፩—፮)

ሐዋርያው እንዳለው በመንፈሳውያን ወላጆቹ መልካም አስተዳደግ የተደረገለት ጢሞቴዎስ በሕፃን ዕድሜው ከታላላቅ የሃይማኖት አባቶችና የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት መካከል አንደኛው ለመሆን አበቃው የወላጅ እናቱ ድንቅ ተጋድሎ የመንፈሳዊ ሥራ ውጤት ይህን የመሰለ የክብር ስም አስገኘለት ። ከእናቱ በወረሰው ንጹህ ጠባይ ራሱ ተመስግኖ ወላጆቹንም አስመሰገነ ። የመንፈሱን ጥንካሬ የአእምሮውን በሳልነት በሚፈጽመው ተግባር ምሳሌነቱን ለሌሎች አሳየ ።

ነቢዩ ኢሳይያስም እንደጢሞቴዎስ እናት ልጆቻቸውን በመንፈስ ፤ በጥበብ የሚያሳድጉ መንፈሳውያን እናቶች ልጆቻቸው ብልህና አስተዋይ ይሆናሉ ። የእግዚአብሔር መንፈስ የጥበብ ና የማስተዋል ፤ የምክርና የኃይል መንፈስ የእውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ያርፍበታል ። እግዚአብሔርን በመፍራት ደስታውን ያያል ። ዓይኑንም እንደምታይ አይፈርድም ። ጆሮውንም እንደምትሰማ አይበይንም ነገር ግን ለድሆች በጽድቅ ይፈርዳል ሲል ተንብዮአል ። በምድርም ግብረ ገብነት ያለውና በመልካም ምግባር ያደገ በትክክል ለሁሉም ፍትሕ ከመስጠት በቀር የማያዳላ መሆኑን አስረድቷል ።

ስለዚህ ወላጆች ልጆቻቸውን በሚገባ ቢያሳድጉ ልጆችም የወላጆቻቸውን ተግሣጽና ምክር እየተቀበሉ በሥርዓት ቢያድጉ ሁለቱም ወገኖች ክብር ሊያገኙበት እን ደሚችሉ አያጠራጥርም ።

ወ/ት መዓዛ አስማማው



www.ethiopianorthodox.org

## ጨዋታና ቁምነገር I

ደመና በዞረ ጊዜ ጨው ይቀልጣል ፤
የሰው ኃጢአት በበዛ ጊዜ የእግዚአብሔር ረድኤት ይርቃል መጽ/ ጨዋታ

“ እሺ ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ የምድርን በረከት
ትበላላችሁ እንቢ ብትሉ ብታምጹም ግን ሠይፍ
ይበላችኋል ፤ ይህን የእግዚአብሔር አፍ ተናግሮአል ።”
— በሬ በቅልጥ— ቅዱቱን ይዞት ይኖራል ። ገና ኋላ ለቁርበቱ ኢሳ ፩፡፲፱
ግልፈያ ይሆነኛል ፤ ብሉ ይሆን ? መጽ - ጨዋታ
የአዳምም ልጆች እንደዚሁ ለተዝካራቸው ያኖራሉ ፤ ዋናው
ዓይናቸው ሲያይ ቢሰጡት ይኩነኑ ይሆን ?
“ብልና ዝገት በሚያጠፉት ፤ ሌቦችም
ቆፍረው በሚሠርቁት ዘንድ ለናንተ በምድር
ላይ መዝገብ አትሰብስቡ ፤ ነገር ግን ብልም
ዝገትም በማያጠፉት ፤ ሌቦችም ቆፍረው በማይ
ሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በሰማይ መዝገብ
ሰብስቡ መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ
በዚያ ይሆናልና” (ማቴ ፤ ፮ ፤ ፲፱—፳፩)
መሳል መልካም ነው ብረትን ይስለዋልና
መጽሐፍም መልካም ነው ልብን ያበራዋልና መጽ- ጨዋታ
“ በመጽናትና መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት
ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈው
ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአል (ሮሜ ፲፭ ፤ ፬ )

ቀሲስ ዳኛቸው ካሣሁን

ጎብር የአማርኛ መወድስ ቅኔ
ከመርዓዊ ጉጉት የቅኔ አብነት

ያዳም ዘሮች ሁሉ ጥቂት ለሥጋ ስንቅ ያዙ ያሳዝናልና ድንገት ስንቅ ያላዘ ሰው ሲነሣ ፤
ርቧችሁም አይቀር አሁን ታደርሳችኋለች ተምሣ ፤
መቃብር የቁልቁለት በቅሎ ገሥግሣ ገሥግሣ ፤
ይችንስ ዓለም አሠር ፈጣን ተላለች ቀራጭ ጭራ ነሥንሣ ነሥንሣ ፤

አዳምንሂ ስታሠርገው መጠጥ አድርገህ አሣሣ
ሞት ሥጋ አሳላፊ ቋሚ የማትረሣ ፤
መቸ ከአጠገብህ መጣሁ ወየሁ ያለብኝ ወቀሣ ፤
ሁሉ ከፊትህ በየጊዜው የዘመድ ቋሚ የለህ ምሣ ።

የቅኔው አቅራቢ ሊቀ ልሳናት ነቅዐ ጥበብ ወንድም

www.ethiopianorthodox.org